# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 265 ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# ‹‹ህወሓት ከህዝብ ጥያቄ እንዳይነሳበት ድክመቱን በጦርነት ሸፍኖ መኖር የሚፈልግ ቡድን ነው ››

- የትህዴን ታጋዮች

መኣርግ ገ/እግዚኣብሔር፣
መሰረት ገ/ዮሃንስን



አቶ አብዳይ ሰኢድ



አቶ ብርሃነ ተስፋይ

አዲስ አበባ፡- የህወሓት ቡድን ሰላም የማይፈልግበት ምክንያት ያልተመለሱ የትግራይ ህዝብ ጥያቄዎች ስላሉት እና ከተጠያቂነት ለማምለጥ እንደሆነ የትግራይ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ታጋዮች ብርሃነ ተስፋይ እና አብዳይ ሰኢድ ገልፀዋል።

አቶ ብርሃነ ተስፋይ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሚታተመው ከወጋሕታ ጋዜጣ በነበራቸው ቆይታ እንደገለፁት፤ ህወሓት ጦርነትን እየመረጠ ያለበት ዋናው ምክንያት ያልተመለሱ የትግራይ ህዝብ ጥያቄዎችን ለማፈን እና አቅጣጫ ለማስቀየር ነው፡፡

እንደ አቶ ብርሃነ ገለጻ፣ ይህ ቡድን ስልጣን ከተቆጣጠረ ጀምሮ በትግራይ ህዝብ ስም እየነገደ የመጣ ነው፤ የትግራይ ህዝብ ልጆቹን በመስዋእትነት የከፈለው ለኢትዮጵያ ህዝቦች እኩልነት፣ ሰላም፣ ፍትህ እና ዴሞክራሲ ሲል ነው። ነገር ግን ህወሓት ይህንን አላማ ወደ ጎን በመተው ህዝቡ ያገኘውን ድል ለራሱ ጥቅም ነው ያዋለው።

ስለሆነም የህወሓት ቡድን ወንጀሉን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሲል የተለያዩ ግጭቶችንና ጦርነቶችን በመፍጠር ዕድሜውን ለማራዘም በመጣር ላይ ይገኛል፡፡

የትግራይን ህዝብ ጥያቄ ላለመመለስ ሲል በተለይም የትግራይ ወጣቶችን እያታለለ እሳት ውስጥ እየማገዳቸው ነው፡፡

ሰላምና መረጋጋት ከተፈጠረ ከኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ከትግራይ ህዝብ የተለያዩ ጥያቄዎች ሊነሱበት እንደሚችሉ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ የትግራይን ህዝብ ከሁሉም አጎራባች ክልሎች ጋር በማጣላት ወንጀሉ መሸፈን እና የስልጣን ዘመኑ እና ጥቅሙ ለማራዘም የሚፈልግ ኃይል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

"ህወሓት ከሕዝብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# "የሲሚንቶ አቅርቦትና ስርጭት በሚያስተጓጉሉ ሳይ የማያዳግም እርምጃ ይወሰዳል"

- የኦሮሚያ ክልል መንግሥት

# "ክልሉ በሲሚንቶ ጉዳይ ሰውሠራሽ ችግሮችን ለመፍታት መወሰኑ ለሌሎችም ተሞክሮ ይሆናል"

የማዕድን ሚኒስቴር

ፍቃዱ ዴሬሳ





ፎቶ ፡- በገባቦ ገብሬ

አቶ አወሉ አብዲ እና ኢንጂነር ታከለ ኡማ

አዲስ አበባ፡- የሲሚንቶ አቅርቦትና ስርጭትን በሚያስተጓጉሉ ሕገወጦች ላይ የማያዳግም እርምጃ እንደሚወስድ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት አስታወቀ። ክልሉ በሲሚንቶ ጉዳይ የሚታዩ ሰውሰራሽ ችግሮችን ለመፍታት መወሰኑ ለሌሎችም ክልሎች ተሞክሮ ይሆናል ሲል ማዕድን ሚኒስቴር ገልጿል።

በኦሮሚያና በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር ጥረት እየተደረገ መሆኑ ተገልጧል።

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትናንት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በግንባታ ቁሳቁሶች በተለይም በሲሚንቶ አቅርቦቶች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እያደረገ መሆኑን አስታውቋል።

የዋጋ ንረቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚስተዋል መሆኑና ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ቢኖሩም በሀገር ውስጥ ተመርተው የዋጋ ጭማሪ ከሚስተዋልባቸው ምርቶች መካከል የሲሚንቶ ምርት አንዱ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወሉ አብዲ ተናግረዋል።

የሲሚንቶ ምርቶች ከፋብሪካዎች የሚወጡበት

"የሲሚንቶ አቅርቦትና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ቻይና በ1 ሺህ 709 ፕሮጀክቶች እየመራች ነው

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- ከሁሉም አገራት በላይ ቻይና በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ዘርፍ በአንድ ሺህ 709 ፕሮጀክቶች ቀዳሚ በመሆን የኢትዮጵያ የልማት አጋርነቷን እያሳየች እንደሆነ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት መረጃ ቡድን መሪና ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር አዛለች በቀለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ቻይና ከየትኛውም አገር በላይ በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ልማት በመሰማራትና 1 ሺህ 709 ፕሮጀክቶችን በማልማት ቀዳሚ የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት አጋር ናት፡፡ ሌሎቹ ሳኡዲ አረቢያና ህንድ በመፈራረቅ ከሁለተኛ እስከ ሶስተኛ ያለውን የአብሮ መልማት ደረጃን በመያዝ በኢንቨስትመንት ሥራ አጋርነታቸውን አስቀጥለዋል፡፡

ዳይሬክተሯ እንደገለጹት በኢትዮጵያ በአንድ ሺህ 709 ፕሮጀክቶችን በማልማት በኢንቨስትመንት ሥራ በተሰማሩ ቻይና ባለሀብቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ፕሮጀክቶች ውስጥ 377 በቅድመ ዝግጅት መሆናቸውን የገለጹት

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# "ኢትዮጵያና አሜሪካ በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ ትብብራቸው እንዲጠናከር እሠራለሁ"

- የአሜሪካ ኮንግረስ አባል ትሬንት ኬሊ

ገጽ 3








ዜና

# ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የሀገር ሽማግሌዎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን የጋሞ አባቶች ገለጹ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**


ሐረር፡- ኢትዮጵያ እየገጠሟት ካሉ ችግሮች እንድትወጣና ሀገራዊ ምክክሩ የታለመለትን ግብ እንዲያሳካ በየአካባቢው ያሉ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን የጋሞ አባቶች ገለጹ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የጋሞ አባቶች፤ በየአካባቢው የሚከሰቱ ግጭቶች ለማስወገድና ሰላም ለማስፈን የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቅርቡ የሚጀመረው ሀገራዊ ምክክር ውጤታማ እንዲሆንም የሀገር ሽማግሌዎችን በአግባቡ ማሳተፍ ይገባል ሲሉ አጽንዖት ሰጥተዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሆደ-ሰፊ መሆን አለበት ያሉት ካዎ በቀለ ብዙነህ ናቸው። ሁሉም ዜጋ ከግለሰባዊ ጥቅሞች ይልቅ ሀገርን በማስቀደም ለኢትዮጵያ የሚበጁ ሥራዎችን ሊሠራ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች አለመግባባቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ሌላ ተጨማሪ ችግሮች እንዳይፈጠሩ የሀገር ሽማግሌዎች በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ያሉት ካዎ በቀለ፤ ወጣቱ ትውልድ የታላላቆቹን ምክርና ተግሳጽ መስማት ይኖርበታል ብለዋል።

ትውልዱ ታሪኩን በአግባቡ ማወቅና ቀደምት እናትና አባቶቻችን ለሀገራቸው ምን ሠርተው አለፉ? የሚለውን በሚገባ አውቆ አሁን ሀገራችን ለገባችበት ችግር መንስዔው ምንድነው ብሎ መመርመር እንዳለበት ጠቁመው፤ ከዚህ አንጻር የሽማግሌዎችና የምሁራን ሚና ከፍተኛ እንደሆነም አስረድተዋል።


ካዎ በቀለ ብዙነህ


አቶ ዮሃንስ ሆሴ

ፎቶ ፡- ዳኜ አበራ

"የቀደምት እናትና አባቶቻችን በጎ ሥራዎችን ማስቀጠልና ሀገራችንን ማሳደግ ሲገባን እዚህ ችግር ውስጥ ለምን ገባን ብለን መመርመር ይኖርብናል" ሲሉ አሳስበዋል።

ሁሉም ሰው ለሰላም ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል ያሉት ካዎ በቀለ፤ የመቻቻል፣ የመፈቃቀር፣ የመዋደድ፣ የመረዳዳትና ሌሎችም የጋራ እሴቶቻችን አጠናክረን ማስቀጠል እንደሚገባም አብራርተዋል።

አቶ ዮሃንስ ሆሴ በበኩላቸው፤ በየአካባቢው የሚፈጠሩ ግጭቶች ለማስወገድና ሰላም ለማስፈን የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን አውቀው በኃላፊነት ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

አቶ ዮሃንስ የጋሞ አባቶችን ተሞክሮ ሲያስረዱ፤ "ግጭቶች ከመፈጠራቸው በፊት ስለግጭት አስከፊነትና ከዚህ በፊት ስለነበሩ ተሞክሮዎች በማስረዳት ኅብረተሰቡ ግጭትን እንዲያወግዝ እናስተምራለን" ብለዋል።

ግጭት ፈጣሪ የሰጠንን ሀብቶቻችን በአግባቡ እንዳንጠቀምና ሌላ የባሰ ችግር ውስጥ እንድንገባ በማድረግ ሀገራዊ እድገታችንን ያቀጭጫል ያሉት አቶ ዮሃንስ፤ በየአካባቢው ተሰሚነት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች በመላው ሀገሪቱ ግጭቶች እንዲጠፉና ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር ሊሰሩ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ወጣቱ ትውልድ የሰላም አስፈላጊነትና የግጭት አውዳሚነት በመገንዘብ ለሰላም ዘብ እንዲቆምና ለሀገሩ እድገት የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።



## ‹‹በአማራ ክልል የተከናወነው ሕግ የማስከበር ሥራ የጠላትን ቅስም የሰበረ ነው ››

**- አቶ ግዛቸው ሙሉነህ**
**የክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ላለፉት ሶስት ሳምንታት የተከናወነው ሕግ የማስከበር ሥራ የጠላትን ቅስም የሰበረ መሆኑን የክልሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አስታወቀ።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ትናንት በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫቸውም፣ ሕገወጥነትና ስርዓት አልበኝነትን በማጀገን ክልሉን የትርምስ ማዕከል ለማድረግ የተወጠነውን ሴራ ማክሸፍ የቻለ የሕግ ማስከበር ሥራ መሠራቱን አንስተዋል።

መንግሥት ሕግና ስርዓት የማስከበር አቅም እንዳጣ በማስመሰል፣ ሕዝባዊ ቁጣ እንዲነሳና ከፍተኛ ሁከት እንዲፈጠር ለማድረግ የተሴረው ሴራ ከሽፏል ነው ያሉት የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊው።

የፀጥታ ኃይሉ ራሱን መስዋዕት በማድረግ ሕግ የማስከበር ተገቢ ሚናውን እየተወጣ መሆኑን ገልጸው፣ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሕዝቡ ከስጋት እፎይ እንዲል ማድረግ መቻሉንም ጠቁመዋል።

ጠላት፣ ብሔርን ከብሔር፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት የማጋጨት ስልትን በመጠቀም በአማራ ክልል ሁከት ለመፍጠር እና ለዳግም ወረራ ክልሉን ለማዳከም ጥረት ቢያደርግም፣ የውስጥ አንድነትን ማረጋገጥ የቻለ የሕግ ማስከበር ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

በጋራ ዘመቻ ሂደቱም በቀጥታ 6 ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎችን ማሳተፍ መቻሉንም ነው አቶ ግዛቸው የገለጹት።

በሕግ ማስከበር ሥራው በክልሉ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር እንዳይኖር መደረጉን እና በሽፍቶች የሚፈፀም ዘረፋና ስርቆትን መቀነስ መቻሉንም ተናግረዋል።

# "የሕዝቡን አንገብጋቢ ችግር ለመፍታት ከመቼውም ጊዜ በላይ በቁርጠኝነት እንሠራለን"

**- ከንቲባ አዳነች አቤቤ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝቡን አንገብጋቢ ችግር ለመፍታት ከመቼውም ጊዜ በላይ በቁርጠኝነት እንሰራለን፤ ሰርተንም እናስረክባለን ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡



ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ እየተገነቡ ያሉ የ60 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል፡፡

በጉብኝታቸው ወቅት እንደገለጹት፣ የሕዝቡን አንገብጋቢ ችግር ለመፍታት ከመቼውም ጊዜ በላይ በቁርጠኝነት እንሰራለን፤ ሰርተንም እናስረክባለን" ብለዋል፡፡

ከንቲባዋ ባደረጉት ጉብኝት፣ የሕዝብ አገልግሎት ዘርፎች፣ የከተማ ማስዋብና የከተማ ግብርና ሥራዎች ያሉበትን ደረጃ ተመልክተዋል።

በጉብኝታቸውም አብዛኞቹ ሥራዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልፀው፣ ለሕዝባችን በገባነው ቃል መሰረት ሌሊትና ቀን ያለ ዕረፍት ሰርተን ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውሉ በማድረግ ወደ ሌላ ሰው ተኮር ተግባራት እንሸጋገራለንም ነው ያሉት።

ግንባታዎችም ሆኑ ሌሎች ሰው ተኮር ተግባራት በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ እንቅፋት የሚሆኑ ማንኛውም ችግሮች ካሉ ከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የሚፈቱበትን አግባብ ለማመቻቸት በተለየ ሁኔታ እየሠራ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

እስካሁን ባለው ሂደትም ለበርካታ ችግሮችና የአሰራር ማነቆዎች መፍትሔ እየሰጡ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ከፕሮጀክት ጉብኝቱ ጎን ለጎንም፣ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ያለውን የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በአገልግሎቱ ዘርፍ የሚታዩ ችግሮችን በወረዳዎች ተገኝተው መመልከታቸውን ከከንቲባ ጽሕፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

ዜና



# ‹‹የሚታየውን የዋጋ ንረት በቀጣይነት ለማስቀረት ማህበራት በቅንጅት መሥራት አለባቸው››

**አቶ አብዲ ሙመድ**
**- የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር**

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- እንደ አገር በሸቀጦች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት በቀጣይነት ለማስቀረት ማህበራት በቅንጅት መስራት እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አብዲ ሙመድ እንደተናገሩት፣ እንደ አገር በሸቀጦች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለማስቀረት ማህበራት በቅንጅት መስራት አለባቸው።

በሸቀጦች ላይ የሚታየውን የዋጋ ንረት ለማስቀረት የኅብረት ሥራ ማህበራት ዋነኛ ተዋናዮች እንደመሆናቸው የእነሱ ተቀናጅቶ መስራት አምራቾችንና ሸማቾች በአማካይ የገበያ ቦታ በማገናኘት ተጠቃሚ ያደርጋል። በሚስተዋለው የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ቅነሳ ላይም ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ሲሉ አቶ አብዲ ተናግረዋል።

ማህበራቱ በሚያደርጉት የቅንጅት ሥራም በሁሉም የሀገራችን ክፍል ዘላቂነት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ አምራቹን እና ሸማቹን ማህበረሰብ ማገናኘት ሊሰሩ ይገባል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ ለማህበራቱ በዘላቂነት እና ቀጣይነት የሚገበያዩበት ዘመናዊ የገበሬዎች የገበያ ማዕከላት በተመረጡ የአዲስ አበባ ቦታዎች ካልተገነቡ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ ንረት አይረጋጋም" ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ማብራሪያ በገበያ ማዕከላት ለግብይት ከሚቀርቡ የግብርና ምርቶች መካከል ጤፍ ፣ ኮረሪማ ፣ ማር ፣ አተር ፣ ምስር ፣ ፍርኖ ዱቄት ፣ በርበሬ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ዝርያዎች፣ በቆሎ፣ የፋብሪካ ምርቶች እና ሌሎች የግብርና ምርቶች ይገኙበታል። እነዚህም መሰረታዊ ፍጆታዎች ከደላላና ተገቢ ካልሆነ የዋጋ ጭማሪ ማህበረሰቡን ለማዳን በሚያስችል መልኩ ማቅረብ ይችላሉ ብለዋል።

እንደ ኮሚሽነር አብዲ ገለጻ፣ አገራችን ከዘርፉ በሰፊው ተጠቃሚ እንድትሆን ለማስቻል አምራቾችም ያላቸውን አቅም አሟጠው ከመጠቀምም ሆነ ሸማቹን እኩል ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ የግብይት እሴት ሰንሰለት ጥናት ትንተና እየተሰራ ነው። በትንተናው የተመላከቱ ምክረ ሃሳቦችን በማቅረብም ለችግሩ መፍትሄ ማግኘት ይቻላል ።

በተለይ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ የተሰማሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከነበሩበት ውስብስብ ችግሮች እንዲወጡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠንካራ ድጋፍና ክትትል በመስጠት መልካም ሥራቸው እንዲጎላ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

# "ኢትዮጵያና አሜሪካ በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ ትብብራቸው እንዲጠናከር እሠራለሁ"

**- የአሜሪካ ኮንግረስ አባል ትሬንት ኬሊ**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና አሜሪካ በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ ትብብራቸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩላቸውን ሚና እንደሚወጡ የአሜሪካ ኮንግረስ አባል ትሬንት ኬሊ ገለፁ።

የኮንግረስ አባል ትሬንት ኬሊ እና የልዑካን ቡድናቸው እንዲሁም በኢትዮጵያ የአሜሪካ ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ትሬሲ አን ጃኮብሰን የብሄራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎትን ዲጂታል ኤግዚቢሽን ጎብኝተዋል።

በጉብኝታቸው ወቅት ኮንግረንስማን ትሬንት ኬሊ እንደገለጹት፣ኢትዮጵያና አሜሪካ በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ በተለይም ደግሞ ሽብርተኝነትና ሌሎች ድንበር-ዘለል ወንጀሎችን በጋራ በመከላከል የቆየና የዳበረ አጋርነት አላቸው።

ይሄው ትብብራቸውም ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩላቸውን ሚና እንደሚወጡም በአጽንኦት ተናግረዋል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል አቶ ተመስገን ጥሩነህ በዚሁ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ የኢትዮጵያና የአሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን ጠቁመው፣ ሀገራቱ አሁንም በተለያዩ የትብብር መስኮች በጋራ እየሰሩ ይገኛሉ ብለዋል።

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ ጠንካራ የአሜሪካ ስትራቴጂክ አጋር መሆኗን ገልጸው፣ ይህን አጋርነት እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ተቋም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እንዲሁም በመረጃና ደኅንነት ዘርፍ ያለውን ትብብር የበለጠ ለማሳደግ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን አውስተዋል።



ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት በተደረገው ሪፎርም፣ አጋርነትና ትብብርን ማጠናከር፣ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ በመሆን ሁሉንም እኩል የሚያገለግል ተቋም ማደራጀት፣ ስትራቴጂክ እይታ ያለው አመራር መገንባት፣ ፕሮፌሽናልና ኢትዮጵያን የሚመስል የሰው ኃይል ማብቃት እንዲሁም የዘመኑን የደኅንነት ስጋት የሚመክቱ የቴክኖሎጂ አቅሞችን ማልማትና መጠቀም መቻሉን አቶ ተመስገን አስረድተዋል።

እስከ አሁን የተከናወኑት እነዚህ ተግባራትም አካባቢያዊና አህጉራዊ ሰላምና ደኅንነትን በማረጋገጥ በኩል መሰረት መሆናቸውን ገልጸው፤ በዚህ ረገድ የአሜሪካ አጋርነት ወሳኝ በመሆኑ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ትብብር ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል።

ኮንግረንስማን ትሬንት ኬሊ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያና አሜሪካ እንደ ሽብርተኝነት ዓይነት ዓለምአቀፋዊ የደኅንነት ስጋቶችን ለመከላከል በጋራ እየሰሩ በመሆናቸው የሁለቱ ሀገራት የመረጃና ደኅንነት ተቋማት የጀመሩት ትብብርና አጋርነት የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩላቸውን ሚና እንደሚወጡ መግለፃቸውን ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ‹‹የአንበሳ አውቶቡስ አገልግሎት አሰጣጥ ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ መጥቷል ››

**-ተሳፋሪዎች**

# ‹‹ አገልግሎት ለማሻሻል ስምሪቱን በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል ››

**አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት**

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የአንበሳ አውቶቡስ አገልግሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ መጥቶ በአሁኑ ወቅት ተሳፋሪዎችን ለእንግልት እየዳረገ መሆኑን በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች ተሳፋሪዎች ገለጹ።

ወጣት ትዕግስት አንተነህ የዘወትር የአንበሳ አውቶቡስ ተጠቃሚ ነች። ወጣት ትዕግስት እንደምትለው የአንበሳ አውቶቡስ ከጊዜ ወደጊዜ አገልግሎቱ እያሽቆለቆለ መጥቷል።አውቶቡሶቹ በሰዓታቸው ካለመምጣታቸውም ባሻገር ሰበብ ፈልገው ለረጅም ሰዓት ቆሞ ሲጠብቃቸው የቆየውን ተሳፋሪ ሳይጭኑ ወደ መጡበት ይመለሳሉ። ሲላቸው ደግሞ ተሳፋሪ በሌለበት ቦታ ተደራርበው በመምጣት ባዷቸውን ጸሐይ ላይ ቆመው ይውላሉ።



የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጠችው አስተያየት በአንዳንድ መስመር ላይ ሰዓታቸውን ጠብቀው የመምጣት ችግር አለ ብላለች። 32፣102፣ 61 የመሳሰሉ ኮተቤ እና ሀያት አካባቢ ረጅም መንገድ የሚሄዱ አንበሳ አውቶቡሶች ረጅም ሰልፍ እና ሰዓት ተጠብቀው የሚገኙ ናቸው ብለዋል።

በርካታ ህዝብ ሲተራመስ እያዩ እንዳላዩ የሚያልፉ ከመኖራቸውም በላይ ተሳፋሪው በሩጫ እየወደቀና እየተነሳ ሲከተላቸው ትተውት እብስ የሚሉ በርካቶች መሆናቸውን ወጣት ትዕግስት ትናገራለች።ፌርማታዎችን ጥሰው የሚያልፉና ተገልጋይ የሚያመናጭቁ መኖራቸውንም አልሸሸገችም።

ሌላዋ ማየት የተሳናት ወጣት ታሳፋሪ ብርቱካን ጌታቸው እንደምትናገረው ባሶች ፌርማታዎች ላይ ሲቆሙ አልፎ አልፎ የደረሱበትን ቦታ በድምጽ የማሰማት ሁኔታ ቢኖርም ሆኖም አሽከርካሪዎቹ ማየት ለተሳናቸው የሚሰጡት የተለየ ግልጋሎት ባለመኖሩ ብዙ ጊዜ በአንበሳ አውቶቡስ ለመጠቀም ፍላጎት በኖራትም አገልግሎቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ አይደለም።

አቶ ሰይፈ ገብረጻዲቅ የተባሉት የአንበሳ አውቶቡስ ደንበኛ በበኩላቸው አንበሳ አውቶቡስ ከመጠን በላይ መጠቅጠቁ አግባብ ባይሆንም ህዝብ ሲቸገር እያዩ አልፈው አለመሄዳቸው እንደሚያስመሰግናቸው ተናግረዋል።

በአንበሳ አውቶቡስ ለመሳፈር ከሁለት እስከ ሶስት ሰዓት ጠብቀው የተሳፈሩበት ጊዜ መኖሩንም ገልጸው፤ ተቆጣጣሪዎች ከዚህ በፊት እንደነበረው ስምሪቱን የሚከታተሉ ባለመሆኑ ክፍተት እየተፈጠረ መሆኑን አስረድተዋል። በተለይ 3 ቁጥር 99 ቁጥር የመሳሰሉት አውቶቡሶች ሾፌሩ የለም፤ቲኬት ቆራጯ አልተገኘችም በሚሉ ውሃ የማይቋጥሩ ምክንያቶች ተገልጋዩ ለእንግልት በተደጋጋሚ እንደሚዳረግ ጠቁመዋል።

በተሳፋሪዎቹ የተነሱትን ቅሬታዎች በተመለከተ ምላሽ የሰጡት የአንበሳ ከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍሬው ሰማ፣ የአውቶቡሶች ከመስመር መስመር መለያየት በየጊዜው እየተስተካከለ ሲሆን በልማት ምክንያት የተቋረጡ መስመሮች አገልግሎት የማስጀመር ሥራ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ከከተማ አስተዳደር እና ከወርልድ ባንክ ጋር በመሆን የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የቁጥጥር፣ የስምሪት እና የክትትል ሂደቱን በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩንም አመላክተዋል።

ቴክኖሎጂዎቹ በሙሉ አቅም ወደ ሥራ ሲገቡ ማየት የተሳናቸውን እና አካልጉዳተኞችን የፌርማታ መረጃ የሚገልጹ አሰራሮች እንደሚኖሩት የገለጹት እስከዚያውም በአውቶቡሶቹ የሚገኙ ማሳያ ጽሁፎች ማየት ለተሳናቸው መረጃ የሚሰጡ ናቸው ብለዋል።

ህዝብ ጭነው የሚሄዱና መዳረሻ ላይ ረጅም ሰዓት ጊዜ የሚያቃጥሉ ስለመኖራቸው ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ይደርሱናል ያሉት ድንገተኛ ተቆጣጣሪዎች በዋና ዋና መስመሮች ፓትሮል እንዲያደርጉ በማድረግ ችግሩን ለመቀነስ እየሰራን ነው ብለዋል። አንዳንዴም በብልሽት ምክንያት የሚቆሙ ሲኖሩ ከሌላ ቦታ አውቶቡሶችን በመመደብ ህብረተሰቡ እንዳይንገላታ ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በኮንዶሚኒየሞች እና ህዝብ በስፋት በሰፈረባቸው አካባቢዎች ከፍ ያለ የአንበሳ የአውቶቡሶች ስርጭት መኖሩን የገለጹት ምክትል ሥራ አስኪያጁ በልማት ምክንያት አገልግሎት የተቋረጠባቸው መስመሮች በከፊል ወደ አገልግሎት የማስገባት ሥራ እየተሰራ ነው ብለዋል።

በመንገድ ሥራ ምክንያት የተቋረጡ ስድስት መስመሮች መልሶ ወደ ሥራ ማስገባታቸውን የተናገሩት ኃላፊው በቀጨኔ፣ በኮተቤ በአቃቂ በመሳሰሉት 8፣ 32፣ 10፣ 72፣ እንዲሁም 25 ቁጥር መስመሮች መንገዶቹ ባይጠናቀቁም ካለው የህብረተሰብ ችግር የተነሳ መስመሮቹ በማያመች ሁኔታም ቢሆን ወደ አገልግሎት ተመልሰዋል ብለዋል። አራት ቁጥር እና ሌሎችም የመንገድ ሁኔታ እየታየ ወደ አገልግሎት እንደሚመለሱ ጠቁመዋል።

በመለዋወጫ ችግር አገልግሎት ምክንያት ያቋረጡ የተበላሹ አውቶቡሶችን በፍጥነት ጠግኖ ወደ ሥራ በማስገባት ሂደት ተግዳሮት መፍጠሩንም ገልጸዋል።ከብሔራዊ ባንክ የሚገኘው ሳንቲም በቂ ባለመሆኑ በሳንቲም እጥረት እየተቸገርን ነው ያሉት ኃላፊው ህብረተሰቡ ዝርዝር ሳንቲሞችን በመያዝ ትብብር እንዲያደርግም ጠይቀዋል።

ከ1923 ዓ.ም የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቱን የጀመረው የአንበሳ ከተማ አውቶቡስ ድርጅት በአዲስ አበባ እና አዲስ አበባ ዙሪያ ከተሞች በሚገኙ 125 መስመሮች በቀን ከ600 ሺህ ህዝብ በላይ እያጓጓዘ ይገኛል።

# ለአብርሆት በተደረጉ ልገሳዎች በግዢም ጭምር ሲገኙ የማይችሉ መጻሕፍት መገኘታቸው ተገለጸ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት በተደረጉ ልገሳዎች በግዢም ጭምር ሊገኙ የማይችሉ መጻሕፍት መገኘታቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ያዘጋጀው ከተማ አቀፍ የንባብ ንቅናቄ ሳምንት መክፈቻ መርሐግብር ትናንትና ተካሂዷል።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሣው እንደገለጹት፤ ከሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ አንድ ሚሊዮን መጻሕፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ በሚል ሃሳብ ለአብርሆት ቤተመጻሕፍት የንባብ ውጤቶችን ለማሰባሰብ በተደረጉ ጥሪዎች በርካቶች ተሳትፈዋል።

እስካሁን በተደረጉ ልገሳዎች በግዢም ሊገኙ የማይችሉ በርካታ መጻሕፍት መገኘታቸውን ዶክተር ሂሩት ገልጸዋል።

ከተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት ከተበረከቱት መጻሕፍትም መካከል የተለያዩ ሳይንስ፣ የታሪክ፣ የምርምርና የሒሳብ እንዲሁም የቴክኖሎጂ መጻሕፍት ይገኙበታል ያሉት ዶክተር ሒሩት፤ ገበያ ላይ ጭምር የጠፉ ህትመቶችን የሚያመጡ ተቋማትና ግለሰቦችም ጥሪታቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል።



ዶክተር ሂሩት ካሣው



ፎቶ ፡- በፀሐይ ንጉሤ

አቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ

ከመጽሐፍ ማሰባሰብ ተግባሩ ባለፈ የንባብን ጥቅም በተመለከተ የሚያስተምሩ ሰዎችን ማግኘት ተችሏል። በርካቶች የንባብን ጥቅም ትውልዱ ይበልጥ እንዲረዳው ለማስቻልና በጉዳዩ ላይ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ በበጎ ፈቃደኝነት እየሠሩ ይገኛል ሲሉ አስታውቀዋል።

አብርሆትን ጨምሮ በተለያዩ ቤተ መጻሕፍቶችና በሌሎችም ምቹ ባልሆኑ ቦታዎች ተማሪዎች፣ ወጣቶችና ሌሎችም የማህበረሰብ ክፍሎች በብዛት ሲያነቡ ይስተዋላል ያሉት ዶክተር ሂሩት፤ ያነበበ ትውልድ ህብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን በጽኑ አለት ላይ ስለሚገነባ ንባብ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በጎ ለውጦች ቢኖሩም በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ግን የአስተሳሰብ ለውጥ ካልመጣ መጽሐፉ ቤተ መጻሕፍት ገብቶ መቀመጡ ብቻ ውጤት ሊያመጣ እንደማይችልም። ትውልዱም የቀረቡለትን መጻሕፍት በማንበብ እራሱንና አገሩን ለመቀየር መነሳት አለበት ብለዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የተሻሉ የንባብ ምቹ ሁኔታዎችን ብንፈጥር የማንበብ ፍላጎት ያለው ትውልድ እንዳለ የሚሳዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም በየወረዳው ያሉ ቤተ መጻሕፍት የተደራጁበት ሁኔታ ግን ማሻሻል ይጠይቃል።

በመሆኑም በየአካባቢው የሚገኙ ቤተ መጻሕፍት በጀት ተይዞላቸው በአዳዲስ መጻሕፍት እንዲሟሉ ሊደረጉና በአግባቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ እያንዳንዱ ወረዳ ቢያንስ አንድ ቤተ መጻሕፍት መኖሩ በከተማዋ ንባብ ጨርሶ እንዳልተረሳ የሚያሳይ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ነገር ግን በአንድ ወረዳ ውስጥ ስንት ምግብ ቤቶችና ስንት ከረንቡላ ቤቶች አሉ ብለን ብናነጻጽር የቤተ መጻሕፍት ቁጥር የሌለ ያክል ያስቆጥረዋል ብለዋል፡፡

በዚህ ረገድ አብርሆትን እንደምሳሌ አድርጎ በየአካባቢው ሰፊ ሥራ መስራት ይጠይቃል፤ ከዚህ ባለፈ ያሉትን ቤተ መጻሕፍት በአስፈላጊ ግብዓቶች እያሟሉ አንባቢያንን መቀበል ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ለአብርሆት ቤተ መጻሕፍት አንድ ሺ መጻሕፍትን ትናንትና አበርክቷል፡፡

# ‹‹ህወሓት ከህዝብ...

ከ1ኛ ገፅ የዞረ

ህወሓት ከህዝብ ጥያቄ እንዳይነሳበት ድክመቱን በጦርነት ሸፍኖ መኖር የሚፈልግ ቡድን ነው ያሉት አቶ ብርሃነ፣ ይህ ቡድን ሊኖር የሚችለው ጦርነት ሲኖር ነው፤ ሰላም ከሆነ ከህዝቡ የሚነሳበት ጥያቄዎች ብዙ ናቸው፤ ሊመልሰው አይችልም፤ ምክንያቱ በትግራይ ህዝብ እና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ብዙ ወንጀል የፈፀመ ድርጅት ነው ብለዋል፡፡

ህወሓት ከዚህ በኋላ የትግራይን ህዝብ ሊጠቅም የሚችል ኃይል አይደለም፤ የሚጠቅመው ቢሆን ኖሮ ከዚህ በፊት ይጠቅመው ነበር። አሁን ደጋግሞ ጦርነት እየሰበከ የትግራይን ህዝብ ለከፋ ተጨማሪ ችግር እየዳረገው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የትግራይ ህዝብ ከየትኛውም ህዝብ ጋር ሰላምና ፍቅርን ነው የሚፈልገው ያሉት አቶ ብርሃነ፣ ይሁን እንጂ የህወሓት መሪዎች ድክመታቸው በጦርነት ለመሸፈን ሲሉ የትግራይ ህዝብ ሰላም አግኝቶ እንዲኖር እና እንዲለወጥ የሚፈልጉ አይደሉም ብለዋል።

የህግ ባለሙያና የትግራይ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ታጋይ አቶ አብዳይ ሰኢድ በበኩላቸው፣ ህወሓት በካርድ ወይም እጅ አውጥቶ የመረጠው አካል የለም፤ ህወሓት በጥይት ነው የመጣ፤ በጥይት የመጣ ኃይል ደሞ ሁሌ ሊኖር የሚችለው በጥይትና በጦርነት ብቻ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

አቶ አብዳይ ከወጋሕታ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለፁት፤ ህወሓት እንደገና ጦርነት ለመክፈት መዘጋጀቱ የሚያስደንቅ አይደለም፤ ታሪኩና መነሻው ጦርነት ነው፡፡

ህወሓት ሊኖር የሚችለው በማሰር፣ በማፈን፣ በመግደል እና በማፈናቀል ነው ያሉት አቶ አብዳይ፣ ይህንን ድርጊት በትግራይ ህዝብና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሲፈፅም መቆየቱን ተናግረዋል።

የህወሓት ቡድን ታንክና ባንክ በእጁ በነበረበት ወቅት ኢትዮጵያንም ሆነ ትግራዋያንን የጠቀመው ነገር የለም ያሉት አቶ አብዳይ ፤ በለውጡ ምክንያት ወደ መቀሌ ከተመለሰ በኋላም ቢሆን ለትግራይ ህዝብ መከራ መሆኑን ተናግረዋል።

ለህወሓት ከዚህ በላይ እድሜ መስጠት ማለት ሌሎች የከፉ ችግሮችን እንዲፈጠር መፍቀድ ነው ያሉት አቶ አብዳይ፤ የፌዴራል መንግሥት በመግባት ቡድኑን ከህዝቡ ነጥሎ እርምጃ ሊወስድበት ይገባል ብለዋል።

ህወሓት የትግራይን ህዝብን የሚፈልገው ችግር ሲገጥመው ብቻ ነው፤ ይህም ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተግባር ታይቷል ብለዋል። ህወሓት ለትግራይ ህዝብ እንኳን አሁን በሰላም ጊዜ አልጠቀመውም ብሏል።

አቶ አብዳይ እንዳሉት ህዝቡ ከዚህ ችግር የሚያወጣው አካል ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የትግራይን ህዝብ ነፃነት የሚፈልግ ሁሉ ከ የትግራይ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህዴን) ጎን እንዲቆም ጥሪ አቅርበዋል።

# በኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገፅ የዞረ

አዛለች፣ 220 ውደ ፕሮጀክት ትግበራ ገብተዋል፡፡ ቀሪዎቹ አንድ ሺህ 112 ሙሉ በሙሉ ምርት ማምረት ሥራ ላይ የገቡ መሆናቸውን አዛለች ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም መነሻቸውን ከወደ ሳኡዲ አረቢያ ያደረጉና በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ሥራ በተሰማሩ ባለሀብቶች እየተሰሩ ያሉ 236 ፕሮጀክቶች አሉ ያሉት አዛለች፣ 52 ፕሮጀክቶች በቅድመ የፕሮጀክት ሥራ ላይ ያሉ ናቸው፡፡

60ዎቹ ፕሮጀክት ወደ ፕሮጀክት ትግበራ ገብተዋል፡፡ ቀሪዎቹ 124 ሙሉ በሙሉ ምርት ማምረት ላይ ያሉ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

አገራቱ ማኑፋክቸሪንግ ልማት፣ በግብርና ልማት፣ በጤና ዘርፍ፣ በትምህርት ልማት፣ በማዕድን ልማት፣ በሆቴልና መስተንግዶ አገልግሎት ዘርፍ፣ በትራንስፖርትና አስጎብኚነት አገልግሎት ዘርፍ፣ በቤት ግንባታ ልማትና ሽያጭ አገልግሎት፣ የተለያዩ ዘርፎችን በማማከር አገልግሎት፣ በማሽነሪ አቅርቦትና ቁሳቁስ ኪራይ፣ በውሃ ቁፋሮና ግንባታ ኮንትራክተርነት በመሳሰሉት የኢንቨስትመንት ዘርፎች በመሰማራት የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት ልማት በማገዝ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ሁሉም ባለሀብቶቹ በተሰማሩት ዘርፍና አካባቢ የሥራ እድልን ይፈጥራሉ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ያመጣሉ፣ የሥራ ባህል ለውውጥን ያግዛሉ፣ አካባቢዎችን ያለማሉ፣ በአካባቢዎቹ በሚያመርቱት ምርትም ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፈው ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን እንደሚያስገኙ ተናግረዋል፡፡

# “የሲሚንቶ አቅርቦትና ስርጭት በሚያስተጓጉሉ...

ከ1ኛ ገፅ የዞረ

ዋጋና ተጠቃሚው ጋር ሲደርሱ በሶስት እጥፍ የሚጨምሩበት ሁኔታ የሚስተዋል መሆኑን ጠቁመው፤ በየመሃሉ የተሰገሰጉ ህገ ወጥ ደላሎች እንዲሁም የአቅርቦት፣ የትራንስፖርትና የግብይት ሰንሰለቶች ህጋዊ አለመሆናቸው ችግሩ እንዲባባስ አድርጎታል ብለዋል።

ችግሩን ለመፍታት በሲሚንቶ ምርት ግብይት ላይ የሚታዩ ሕገወጦች ላይ እርምጃ እንደተወሰደ አቶ አወሉ ገልጸዋል።

ከምርት አንስቶ ተጠቃሚው ጋር እስኪደርስ ያለውን ሰንሰለት የተቆጣጠሩ አካላትን በማጣራት እንዲወጡ ተደርጓል። በተመሳሳይ በህጋዊ መንገድ የተደራጁ ከሶስት ሺህ በላይ ሥራአጥ ወጣቶች ሲሚንቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው የማድረስ ተግባር እንዲያከናውን እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በክልሉ በሚገኙ ኬላዎች ውጪ በህገወጥ መንገድ ቀረጥ የሚያስከፍሉ አካላት በመኖራቸው ይህን ድርጊት ለማስቀረት ወደ እርምጃ ተገብቷል ሲሉ ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ክልል ከግል አልሚዎችና ባለሀብቶች ጋር በመሆን የትራንስፖርትና የግብይት ስርዓቱ ላይ አሰራሮችን እንደሚዘረጋ አስታውቋል።

በሌላ በኩል ምርት እንዲቀንስ የሚያደርጉ አካላት ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ በማድረግ ችግር እንደሚፈጥሩ አቶ አወሉ ጠቁመዋል።

በተለይ የፀጥታ ችግር በመፍጠር ሥራዎችን የሚያስተጓጉሉ ኃይሎች በመኖራቸው ይህን ችግር ሙሉ በሙሉ ለማስተካከል መንግሥት ወደ ሥራ ገብቶ የማስተካከያ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ገልጸዋል።

በአንጻሩ በውስጣዊ ችግር ምክንያት የፋብሪካዎች የማምረት አቅም ማነስና ሆን ብሎ ምርትን የማስተጓጎል ሥራዎች ላይ የተሰማሩ አካላትን በመለየት እርምጃ በመወሰዱ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ወደማምረት እየተሸጋገሩ መሆኑን አቶ አወሉ ጠቁመዋል። ፡

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ በበኩላቸው በዘርፉ ላይ ከሚደረገው ቁጥጥር አንጻር የኦሮሚያ ክልል ቅድሚያ ሰጥቶ እየወሰደ ያለው እርምጃ አበረታች መሆኑን ተናግረዋል።

ክልሉ ህጋዊ ያልሆኑ ሰው ሰራሽ ችግሮችን ለመፍታትና በፍጥነት ወደ ተግባር ለመግባት ያሳየው ቁርጠኝነት ለሌሎች ክልሎች ተሞክሮ እንደሚሆን የተናገሩት ሚኒስትሩ፣ እርምጃው ከምርት ጀምሮ እስከ ተጠቃሚው እስኪደርስ የሚያስተጓጉሉ አካላትን ለመቆጣጠር ይረዳል ብለዋል።

አሁን ያሉት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት በትክክለኛው መንገድ ወደ ተጠቃሚው መድረስ አለበት። ግብአቶች በህገወጥ ኬላዎች ሳይስተጓጎሉ መቅረብ አለባቸው። ፋብሪካዎችም በሙሉ አቅማቸው ማምረት ይኖርባቸዋል ፤ ለዚህ ደግሞ ጥብቅ ክትትል ያስፈልጋል ሲሉ ኢንጂነር ታከለ ተናግረዋል።

በዕለቱ የሲሚንቶ ፋብሪካ ባለሀብቶችና ተወካዮች እንዲሁም ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ አካላት የሲሚንቶን ምርትና ግብይት ስርዓት ለማሳለጥ የሚረዳ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትህነግ ምስራቅ አፍሪካን የማተራመስ እቅድ መምከን ይኖርበታል!

አሸባሪው ትህነግ በኢትዮጵያና ኢትጵያውያን ላይ ያልፈጸመው የሽብር ድርጊት የለም። የአፍራሽ ተልእኮ ተባባሪዎቹን በመላ ኢትዮጵያ አሰማርቶ ንጹኃንን በአሰቃቂ ሁኔታ ጨፍጭፏል፤ ሚሊዮኖችን አፈናቅሏል፤ የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ የዜጎችን ሀብት ንብረት አውድሟል፤ አስወድሟል።

በሽብር ተግባሩ እና በአገር ክህደት ድርጊቱ እስከ ሰሜን ሸዋ ተጉዞ የነበረው ይህ ኃይል፤ አይቀጡ ተቀጥቶ ከሰሜን ሸዋ ከተመለሰ በኋላም አርፎ አልተቀመጠም፤ የሽብር ተግባሩን በረጃጅም እጆቹ ቀጥሏል፤ በተላላኪው ሸኔ እና ሌሎች የጥፋት ኃይሎች ሀገር እንዳትረጋጋ እየሰራ ይገኛል።

እነዚህ ሁለት ቡድኖች የጥፋት ተልእኳቸውን ለመፈጸም በጎረቤት ሀገሮች ጭምር መሽገው ሰርተዋል። ትህነግ ሱዳን ያደገ የጎለመሰና የጃጀባት ነች። ኢትዮጵያን መውጋት አሀዱ ያለው ሱዳን ተቀምጦ ነው። ዛሬም የኢትዮጵያን መሬት በወረራ ከያዘችው ሱዳን  ጋር እየሰራ ነው። በማይካድራ አያሌ ንጹኃን የጨፈጨፈው ሳምሪ የተሰኘው የትህነግ ገዳይ ቡድን ያለው በሱዳን ነው። አሁንም አንድ እግሩን ሱዳን በሚገኘው የስደተኞች ጣቢያ፣ ሌላውን በወታደራዊ ካምፕ እያደረገ በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሞክሮ ተደምስሷል። የህዳሴ ግድብ ግንባታን ለማስተጓጎል የሚንቀሳቀሱ ሀይሎችም በዚሁ አግባብ ነው።

ኢትዮጵያ ለጥቃት የመጣውን ሀይል ሁሉ እየደመሰሰች በአካባቢው ያለውን ሁኔታ በጽሞና እየተከታተለች ትገኛለች። መሬቷ በሱዳን በሀይል ተይዞባትም ዲፕሎማሲያዊ አማራጮችን ከመጠቀም ውጪ እስከ አሁን ወደ ወታደራዊ እርምጃ አልገባችም። በዚህ መልኩ ከሽብርተኞች ጋር እየተናበቡ የሚፈጸመው የጥፋት መንገድ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና  አሳሳቢ ደረጃ ውስጥ መግባቱን ያመለክታል። ይህ ሁሉ የሆነው ደግሞ ትህነግ በሱዳን መሽጎ እያካሄደ ባለው ሽብርና ጥፋት ምክንያት ነው።

የትህነግ የሽብር ተግባር በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም ። ሰሞኑን ከሚወጡ መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ኤርትራንም እየተነኮሰ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ አካባቢው የጦርነት ስጋት እንዲያንዣብበት የማድረግ አካሄድ ነው። የአሸባሪው ትህነግ ኤርትራን የኢላማው አካል ማድረጉም በምስራቅ አፍሪካ ስጋት የመፍጠር ጉዞውን ያሳያል።

ትህነግ ኢትዮጵያን ሰላም ለመንሳት በሀገር ውስጥና  በሱዳን ጭምር ተቀምጦ እያካሄደ ያለው የሽብር ተግባር፣ ኤርትራን ለመውጋት ጦር እየሰበቀ መሆኑ፣ ኢትዮጵያን ለማተራመስ የውስጥና የውጭ ሀይሎች ጋር በመሆን እያከናወነ ያለው የጥፋት ተግባር  የምስራቅ አፍሪካም ስጋት እስከ መሆን መድረሱን ያሳያል።

እንደሚታወቀው፤ ቡድኑ ህልውናው የተመሰረተው በጦርነት እና በሽብር ተግባር ነው። አንድም ቀን ያለ ጦርነት ውሎ ሊያደር እንደማይችል በሚገባ ይታወቃል። እንዲህ ያለ ኃይል ደግሞ ቃጣናው እንዳይረጋጋ በማድረግ በቁጥጥራቸው ስር ማዋል ለሚፈልጉ አካላት የማይከፍለው መስዋእትነት አይኖርም፤ ካለፉት የሀገር ክህደት ተግባሮቹ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው።

የጥፋት አላማውን ለማሳካት ሲል ሀገር ሸጧል። የሀገር ሉኣላዊነትን ደፍሯል፤ አስደፍሯል፤ ሱዳን የኢትዮጵያን መሬት የያዘችው ትህነግ በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ክህደት ተከትሎ ነው። መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል እንዲሉ ይህ ሀገር የሸጠ ቡድን አሁንም የምስራቅ አፍሪካን ቀጠና ከመሸጥ አይመለስም። አላማውን ለማሳካት ሲል ጠላቴ ይላቸው ከነበሩት ጋር ጭምር ጥምረት ፈጥሮ ሀገር የወጋ ቡድን እንደመሆኑ እንደ አልሸባብ ካሉት አሸባሪዎች ጋር በመሆን ቀጣናውን ከማመስ ይቆጠባል ተብሎ አይታሰብም።

የዚህ ቡድን ፍላጎት በአስቸኳይ ካልተቀጨ የምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ችግር ውስጥ ይወድቃል። እንደሚታወቀው አካባቢው በተለያዩ ኃይሎች ይፈለጋል። የዓለም ሸቀጦች በብዛት የሚተላለፍበት የቀይ ባህር መገኛ መሆኑን ተከትሎ  በኢኮኖሚ ፈረጠምን የሚሉ ሀገሮች በአንድም ይሁን በሌላ ይህን አካባቢ በትኩረት እየተመለከቱት ናቸው። በአካባቢው የጦር ሰፈር መገንባት፣ ከሀገሮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ማድረግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች በርክተዋል።

ይህን አካባቢ  መቆጣጠር የሚፈልጉት ያደጉት ሀገሮች ብቻ አይደሉም፤ አሸባሪዎች፣ የአደገኛ እጽ አዘዋዋሪዎች እንዲሁም ኮንትሮባንዲስቶችምና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተዋንያንም ናቸው። የመርከብ ዘረፋ፣ ዜጎች ህገወጥ አዘዋዋሪዎች ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚላኩበት አካባቢ እንደነበር ይታወቃል። እነዚህ አካላት አካባቢው ሰላም ከሆነ ህልውናቸው እንደሚያበቃ ስለሚያውቁ አካባቢውን ከማመስ ለአፍታም አይታቀቡም። አካባቢው እንዲረጋጋ የማይፈልጉ ሌሎች ሀይሎችም ለእነዚህ ቡድኖች ድጋፍ በማድረግ አፈርጥመዋቸዋል። የአልሸባብ በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ መታየትም ከዚሁ የመነጨ ሳይሆን አይቀርም ብሎ መውሰድ ይቻላል። የዚህ ቡድን አምሳያ እየሆነ ያለው አሸባሪው ትህነግ በምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች በተለያዩ መልኩ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የቀጠናው ፈተና እንደሚሆን መገመት ያስችላል።

ኢትዮጵያ የዚህ አሸባሪ ቡድን ፍላጎት እንዳይሳካ ስታደርግ ቆይታለች። በብሔር እና በሃይማኖት ሰበብ ግጭትና አለመግባባት በመፍጠር መንግሥት ደካማ ለማድረግ የሄደበት መንገድ እንዳይሳካ ተደርጓል፤ ኢትዮጵያውያን ተቻችለው መኖራቸው እኩይ ሴራውን አምክነውታል። ኢትዮጵያ ይህን ቡድን ደጋግማ ሰባብራዋለች፤ አሁንም ይህንኑ ትቀጥላለች። አሁንም ህልሙ እንዳይሳካ ታደርጋለች። ሆኖም አሸባሪ ቡድኖች ድንበር የማያግዳቸው እንደመሆናቸው፤ እነሱን  ለማጥፋት የሚደረገው ትግልም የሀገሮችንና የመላ ዓለምን የተቀናጀ ስራ፤ ከኢትዮጵያ ጎን መቆምን ይፈልጋል። ይሄን በማድረግም የትህነግ የምስራቅ አፍሪካን የማተራመስ እቅድ ማምከን ይገባል።

---

ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

## የመከኑት ስታዲየሞቻችን!

ውቤ ክልደታ

ሰላም እንዴት ሰነበታችሁ ውድ የአዲስ ዘመን ቤተሰቦች፤ ለመሆኑ ሳምንቱ እንዴት አለፈ፤ በተለይ የእግር ኳስ አፍቃሪ ወዳጆቼ ሰሞኑን በአውሮፓ ቻምፒየንስ ሊግ ጨዋታ ላይ ትኩረታቸውን አድርገው መሰንበታቸውን ታዝቤአለሁ። ሊቨርፑል እና ሪያል ማድሪድ ያደረጉት የቻምፒዮንስ ሊግ የፍጻሜ ውድድር ብዙዎችን ትኩረት ስቦ ሰንብቷል።

ስለአውሮፓ ቻፒዮንስ ሊግ ሳነሳ በዚህ ዙሪያ ትንታኔ አልያም ሃሳብ ለመስጠት ፈልጌ እንዳልሆነ ከወዲሁ ተረዱልኝ። ለዚህ የሚሆን ብቃቱ የለኝም። ነገር ግን ከዚህ ጋር የተገናኘ ትዝብት ስላለኝ ነው ብዕሬን ከወረቀት ያዋደድኩት። እንደው ግን ጎበዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ እግር ኳስን ምን ያህል ይወዳል? የራሱ ጠንካራ ክለብ ወይም ቡድን ቢያገኝና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ቢሆን ስንቱ በደስታ ራሱን ይስት ይሆን? ለማኛውም የኔ ትዝብት ከእግር ኳስ ስታዲየሞች ግንባታ ላይ ያተኮረ ነውና እንካችሁ።

በቅርቡ የአፍሪካ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የኢትዮጵያ ስታዲየሞች መስፈርን ማሟላት ስለማይችሉ ውድድር ማስተናገድ አይችሉም የሚል ውሳኔ ማሳለፉ ይታወሳል። በዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የምታደርገው የደርሶ መልስ ጨዋታ ከሀገሯ ውጭ እንዲካሄድ መወሰኑን ሰምተን ብዙዎቻችን ማዘናችን የሚታወስ ነው። የአፍሪካ ዋንጫ መስራች ለሆነች ሀገር ደግሞ ይህ ትልቅ ተቃርኖ ነው። ጨዋታ እንኳ ለማስተናገድ አትችልም መባሉ ምን ያህል እንደሚያም መገመት አይከብድም።

በአንጻሩ ከኢትዮጵያ በብዙ ጊዜ ዘግይተው እግር ኳስን የጀመሩና በሥልጣኔና ታሪካዊ እድገትም በብዙ እጥፍ ከኢትዮጵያ የሚያንሱ ሀገራት በእግር ኳሱም ሆነ በእግር ኳስ ማዘውተሪያ ስፍራዎቻቸው ጥለውን ሲሄዱ ማየት እጅግ የሚያም ነው። እንደው ግን እና የአፍሪካ እግር ኳስ መስራች ሆነን ቢያንስ የአፍሪካ ዋንጫን ማንሳት እንኳን ከበደን ብንል እንዴት ጨዋታ ማስተናገድ የሚችል መጫወቻ ሜዳ እንጣ?

በጣም አሳዛኙና አሁንም መንግሥት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ደግሞ ሀገሪቷ ለዚህ የሚሆን ገንዘብ ከካዝናዋ ማውጣቷ ነው። ይህ ሁለት ሃሳብ አይጋጭም ወይ ለምትሉ ደግሞ መረጃውን በጥቂቱ እንካችሁ።

ከኢትዮጵያ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ያገኘሁት መረጃ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ በአጠቃላይ 16 ስታዲየሞች በግንባታ ላይ ይገኛሉ። ከፊሎቹም በእድሳትና ጥገና ሥራ ላይ ይገኛሉ። ለነዚህ ስታዲየሞች ግንባታ ደግሞ በአጠቃላይ 18 ቢሊዮን 450 ሚሊዮን ብር በጀት ወጪ ተደርጎባቸዋል። ከዚህ ውጭ ደግሞ ለመገንባት ለታቀዱት ስታዲየሞች በድምሩ 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በጀት ተይዞላቸዋል። ይህ እግዲህ በአጠቃላይ ለስታዲየሞች ግንባታ 23 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ መያዙን ነው።

ሀገራችን አሁን ካለችበት የኢኮኖሚ ችግር እና እንደሀገር ከገጠመን የበጀት እጥረት አንጻር ይህ ገንዘብ ከልክ በላይ ብዙ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ታዲያ እኛ ከሁሉም መሆን ያቃተን መሆኑ ደግሞ ትልቅ ህመም የሚፈጥር ነው። አንድም ገንዘባችንን ለሌላ ኢኮኖሚያዊ ችግራችን አላዋልን፤ አልያም የምንመኘውን ስታዲየም ገንብተን በሜዳችን ውድድር ለማድረግ አልቻልንም።

ለመሆኑ በሌሎች ሀገራት ያሉ እና የካፍን መስፈርት የሚያሟሉ ስታዲየሞች ምን ያህል ወጪ ተደርጎባቸዋል ብለን ብጠይቅ የማንገኘው መረጃ እጅጉን የሚገርም ነው። ምክንያቱያም እኛ ከያዝነው ገንዘብ በብዙ ያነሰ ሆኖ እናገኘዋለንና። ለምሳሌ ለአፍሪካ ዋንጫ ብቁ ነው የተባለው የማላዊ ቢንጉ ስታዲየም 78 ሚሊዮን ዶላር የወጣበት ነው። ይህ በኢትዮጵያ ገንዘብ ብንመነዝረው አሁን ባለው የውጭ ምንዛሪ እንኳን አራት ቢሊዮን ብር ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት እኛ ለስታዲየሞች ግንባታ የመደብነው ገንዘብ ይህንን የማላዊ አይነት በትንሹ አምስት ስታዲየሞችን ገንብቶ ሌላ ተጨማሪ ለስፖርተኞች ማጠናከሪያ በጀት ይኖረን ነበር ማለት ነው።

ወደሌሎች የአፍሪካ ስታዲየሞች ስንመጣ የካፍን መስፈርት ማሟላት የሚችለው የትሪፖሊ ስታዲየም የተገነባው በ2 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ነው። በአጠቃላይ አፍሪካ ውስጥ የተገነቡት ደረጃቸውን የጠበቁ ስታዲየሞች ግንባታ የወጣባቸው ገንዘብ ሲታይ ኢትዮጵያ ለስታዲየሞች ግንባታ ብላ ካፈሰሰችው ገንዘብ በብዙ መጠን የሚያንስ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም። ታላላቆቹ የአውሮፓ ስታዲየሞችም ቢሆኑ የወጣባቸው ገንዘብ ሲታይ አሁን ኢትዮጵያ ከያዘችው ገንዘብ የሚስተካከሉ እንጂ የሚበልጡ እንዳልሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለምሳሌ የሳንቲያጎ በርናባው ስታዲየም የወጣበት ገንዘብ 500 ሚሊዮን ዩሮ ነው።

የሚያሳዝነው ደግሞ እነዚህ የሀገራችን ስታዲየሞች አብዛኞቹ ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቁ መፈራረስ ላይ የሚገኙ መሆናቸው ነው። ለአብነትም በአፋር ሰመራ ከተማ ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣበት ስታዲየም ሳይጠናቀቅ በመቆሙ በአሁኑ ወቅት በመፈራረስ ላይ ይገኛል። ስታዲየሙ የተገነባበት ስፍራ ከፍተኛ ሙቀት ያለበት ቢሆንም ግንባው ይህንን ከግምት ያስገባ ባለመሆኑም መስታወቶቹ ረጋግፈው እና ግንቡም ተሰነጣጥቆ ይታያል። ከዚህም አልፎ ስታዲየሙ ጨዋታ የማይደረግበት በመሆኑ ያን ያህል ገንዘብ የወጣበት ስታዲየም ከጥቅም ውጭ እየሆነ ነው።

ልክ እንዲሁ ሌሎቹም በተለያዩ ምክንያቶች የቆሙ አልያም ለመፈራረስ በቋፍ ላይ ያሉ ናቸው። ለዚህ ደግሞ በአብዛኛው የሚነሳው ችግር አንድም የበጀት እጥረት ሲሆን በሌላም በኩል ኮንትራክተሮቹ ጥለው በመሄዳቸው እንደሆነ ይነሳል።

በአጠቃላይ ግን እኛ ከሁለት ያጣን ሆነን መቅረታችን የሚያሳዝን ነው። ወይ ገንዘባችንን ለሌላ ዓላማ አልተጠቀምን፤ አልያም ስታዲየም ገንብተን ለስፖርታዊ ፍላጎታችን ማርኪያ አላዋልን።

እነዚህ ለስፖርት ትኩረት የነፈጉ አካላት እንዲረዱት የምሻው ነገር ስፖርት በራሱ ከመዝናኛነትም ባለፈ የእድገት ምንጭ መሆኑን ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ አይነት በርካታ የእግር ኳስ አፍቃሪ ባለባት አገር ይህንን የስፖርት ዘርፍ በአግባቡ መደገፍ ከስፖርቱም ባሻገር ለሀገራዊ እድገት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ የጣልያኗ ናፖሊ ያደገችው በማራዶና የኳስ ጥበብ የተነሳ እንደሆነ አይዘነጋም።   በአውሮፓም እግር ኳስ በጀት ምን ያህል ከራሳቸው አልፎ በዓለም ላይ ተጽዕኖ እየፈጠረ እንደሆነ እንገነዘባለን።

እኛ ደግሞ ስፖርቱን ቀድመን የተቀበልን፤ ነገር ግን ቶሎ ብለን ለመግደል የሮጥን እንዳንሆን ዛሬም እድሉ በእጃችን አለና ትኩረት ባንነፍገው መልካም ነው። ዛሬ ላይ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርም እነዚህ በብዙ ቢሊዮን የወጣባቸው ስታዲየሞች ግንባታ የት ደረሰ ብሎ ተከታትሎ ቢያስጨርስ እና ለሀገራችን ስፖርት እድገት የራሱን አስተዋፅኦ ቢያበረክት ነገ ከሚመጣ የሞራልም ሆነ የትውልድ ተጠያቂነት ይድናልና  ቢታሰብበት መልካም ነው።

---

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ያልተዘጋው ዶሴ

እንደማንኛውም ሕዝብና አገር ብዙ ያልተዘጉና ለውሳኔ በእንጥልጥል ያሉ ዶሴዎች አሉን። አንዳንዶች በይፋ ባንነጋገርባቸውም በጥቅሻ ተግባብተን በይደር ያቆየናቸው ናቸው። ሌሎቹ ብንከፍታቸው እንደ ፓንዶራ ሙዳይ በውስጣቸው ተዘግተው የነበሩ የከፋት ጣኦታት ሁሉ እያፈተለኩ ወጥተው በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ ይሆኑብናል። አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ አሸባሪው ትህነግ/ ሕወሓት ስድ የለቀቅናቸው ይገኙበታል። ወደድንም ጠላንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሕወሓት አማራጭ እያሳጣን ነው። ስለሆነም የቀረን አማራጭ የማያዳግም መውጫችንን ማማተር ነው። አዎ ! የሕወሓትን የዳጎሰ ዶሴ የመዝጋትን ሒደት የጀመርን ቢሆንም ውጫዊም ውስጣዊ በሆኑ ምክንያቶች የተነሳ በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት በማያዳግም ሁኔታ እየዘጋነው አይደለም። እያደር አዳዲስ ገጾችን እየጨመረብን ነው።

ግልጽ የሆነ የመውጫ ስትራቴጂም ያለን አይመስልም። በዘገየን ቁጥር የሚያስከፍለን ዋጋ እየጨመረ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። ላለፉት 50 አመታት ቢያንስ ሁለት ትውልድ በምንም ሊተመንና ሊገለጽ የማይችል ለዛውም አዋጭ ላልሆነ አላማ ውድ ዋጋ ከፍሏል። በእኛ ይለፍ ወይም ይብቃ ብለን ለሶስተኛ ትውልድ እንዳይተላለፍ ተቀናጅተን ሌት ተቀን መስራት ይጠበቅብናል። ይህን ታሪካዊ ኃላፊነት መወጣት ካልቻልን ነገ ትውልድም ታሪክም ይወቅሰናል። አገርም ትከሰናለች። ከዚህ ያልተዘጋ ዶሴ አንድ አንድ ጥቋቁር ገጾችን ስለ ግንቦት 20 በአለፍ ገደም እንግለጥ።

ግንቦት 20 በግልብ ትንተናና በፈጠራ ትርክት ድቡሽት ላይ የተመሰረተ አማጺና አንጋች ለገዥነት ያበቃ የቀን ጎዶሎና ጥቁር ገጽ ነው። አገራችን ዛሬ ለምትገኝባቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች መባቻም ነው። እንደ አገር እንደ ሕዝብ የገባንበት ቅርቃር አሀዱ፣ ክለቱ፣ ...የተባለበት ቀን ነው ማለት ይቻላል። አምባገነናዊውን የጊዜያዊ ወታደራዊ አገዛዝ /ደርግ/ን ገርስሶ በሌላ ዘራፊ፣ አምባገነንና አፋኝ አገዛዝ በመተካት አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት ዕለት ነው። የተማሪዎችን አብዮት ቀምቶ ስልጣን የጨበጠ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ወደ 70ሺ የሚጠጉ ታጋዮች የተሰውለትን፣ ከ120ሺህ በላይ አካል ጉዳተኛ የሆኑለትን የነጻነት አብዮት ቤተሰባዊ በሆነ ቡድን ጠልፎና አግቶ ስልጣን በመዳፉ ያደረገበት ክፉ ቀን ነው።

የ3ሺህ አመትና ከዚያ በላይ ታሪካችን ወደ 100 አመት የወረደበት፣ ጥንታዊው የአገረ መንግስት ታሪካችን የተካደበት፣ ስንቶች በዱር በገደሉ የተዋደቁለት ሰንደቅ ጨርቅ ተብሎ ዱቄት የተቋጠረበት፣ ጥላቻና ልዩነት የተቀነቀነበት፤ የጋራ ታሪክ፣ ብሔራዊ ጀግናና ምልክት /አይከን/ እንዳይኖረን የታወጀበት፤ አገራዊና ሕዝባዊ አንድነት የተወገዘበት ጥቁር ቀን ነው።

ግንቦት 20 የአገር ሀብት በጥቂቶች እጅ የገባበት፣ እንደ ኤፈርት ያሉ ድርጅቶችና ቡድኖች እንዳሻቸው እንዲዘርፉ ካዝና የተከፈተበት፣ ለዘመናት የተገነቡ ተቋማትና እሴቶች እንዲወድሙ ደማሚት የተቀበረበት፣ ዜጎች እርስ በርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩ የሚሰራ ተቋም የተመሰረተበት፤ ከአንድነት ይልቅ ልዩነት ሕዝብ በጎሳ፣ በሃይማኖትና በሌሎች ማንነቶች እንዲከፋፈል የተሴረበት፣ በጎሳና በቋንቋ ብቻ የተመሰረተው የልዩነትና የጥል የባቢሎን ግንብ / ክልል/ መሰረተ ድንጋይ የተጣለበት፣ አገር ለብተና የታጨችበት፣ አገር በደም ካሳና በእዳ የተያዘችበትና የታገተችበት፣ አናሳዎችና ህዳጣን በአፈሙዝ ብዙኃኑን ቀጥቅጠው የገዙበት፣ አንደኛና ሁለተኛ ዜጋ የተፈጠረበት፣ ወዘተረፈ የሀዘን ቀን ነው። ታሪክ የአሽናፊው ነው እንዲሉ ይህ ሁሉ ቀውስ ውድቀት መወገዝ ሲገባው እንደ ድል በዓል የሚከበረበት ቀን ነው። የሚያሳዝነው ዛሬም ከቀን መቁጠሪያው አለመፋቁ ነው።

ቀኑ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ተስፋ ሳይውል ሳያድር ወደ ቀቢጸ ተስፋነት የቀየረ መናጢ ቀን ነው ማለት ይቻላል። ለ17 አመታት በተካሄደ የእርስበርስ ጦርነት በሁለቱም ወገኖች አምራቹና ወጣቱ የሰው ኃይል በግዳጅና በወዶ ገብነት ለጦርነቱ ተማግዷል። የአገር ሀብት፣ ጥሪት፣ ኢኮኖሚና መሰረተ ልማቶች ወድመዋል። የአገሪቱ እድገት አሽቆልቁላል። ድህነት፣ ኋላ ቀርነትና ማህበራዊ ቀውስ ተንሰራፍቷል። የሚያሳዝነው ይህ ሁሉ ዋጋ የተከፈለለት “ትግል” ገና ከጅምሩ መጨንገፉ ነው። ነጻነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ እኩልነትንና ዴሞክራሲያዊነትን ያዋልዳል ተብሎ የተጠበቀው ጽንስ ውርዴ ሆኖ ቀርቷል። በተለይ ከ1987 ዓ.ም ወዲህ እስከ ለውጡ ዋዜማ በፅኑ ሕሙማን ማቆያ/ICU/ በጠመንጃ በአፈና እና በከፋፍለህ ግዛ የቅኝ ገዥዎች መርህ ቆዩ እንጂ የተነሳለትን አላማ ገና ከመነሻው የዘነጋ ስለነበር ህልውና አልነበረም።

በግንቦት 20፣ ለቀደሙት 27 አመታት ስልጣን ላይ የነበረው ገዥ ፓርቲ ሕወሓት /ኢህአዴግ መመጻደቂያዎች ቀዳሚው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን እኩልነት አረጋግጫለሁ፤ በማንነታቸው እንዲኮሩ አድርጌያለሁ የሚል ቢሆንም የግንባሩ አስኳል የሆነው ትህነግ በሚመራው የትግራይ ክልል በዞኖች እንኳን እኩልነት አልነበረም። ሕዝቡም በአንድ ለአምስት ተጠርንፎ ዛሬ ድረስ ከኢትዮጵያውያን ተለይቶ በጭቆና ፍዳውን እየበላ ይገኛል። ልጆቹን ገብሮ ያለጧሪ ቀባሪ ቀርቶ ለስልጣን ያበቃው ቤተሰባዊ ቡድን ዛሬም ከትክሻው የመውረድ ፍላጎት የሌለውና ይህ አልበቃ ብሎት ኢኮኖሚውን ከጅምላ ንግድ እስከ ጉልት ተቆጣጥሮ፤ መሬቱን፣ የተፈጥሮ ሀብቱንና ጉልበቱን እየዘረፈ ለምሬትና ለብሶት ዳርጎታል።

ለ44 አመታት ማለትም 17 አመታት በትጥቅ ትግል 27 አመታት በገዢ ፓርቲነት በአገር፣ በትውልድና በተቋማት ላይ የተከለው መርዛማ ሰንኮፍ ሳይነቀልና ሳይሽር፤ ከማዕከላዊ መንግስት በሕዝባዊ አመጽና ከውስጡ በወጡ የለውጥ ኃይሎች በልክህ ሁን ተብሎ ሲሰፋ ድምጹን አጥፍቶ ኮሽታ ሳያሰማና ጭራውን ቆልፎ ወደ መማጸኛ ከተማው መቀሌ በመመሸግ፤ በአራቱ የአገሪቱ ማዕዘናት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ግጭቶችንና ቀውሶችን በመቀፍቀፍ በሰንኮፉ ሌላ ሰንኮፍ፣ በእባጩ ላይ ሌላ እባጭ መጨመሩን በጀ ብሎ ተያያዘው። በዚህም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ከቀያቸው ከቤት ንብረታቸው ተፈናቀሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሐን በግፍ ተጨፈጨፉ፤ ሀብት ንብረታቸው ተዘረፈ። በስንት ላብና ሀብት ለአመታት የተገነቡ ከተሞች በእሳት ጋዩ። ለመስማት የሚሰቀጥጡ፣ ለማየት የሚዘገንኑ አረመኔያዊ ድርጊቶች ተፈጸሙ። እንደሀገር ይዘነው የመጣነውን የልቦና ውቅር መለስ ብለን እንድንመረምር አስገደደን።

ሕወሓት ይሄን ሁሉ ሰቆቃ የሚፈጽመው በአምሳሉ በቀፈቀፋቸው ተላላኪዎቹና ቡችሎቹ እየታገዘ ነው። በአናቱ በዩኒቨርሲቲዎች ማንነት ላይ የተመሠረቱ ግጭቶችን በመጎንቆል አገሪቱን ወደማያባራ የእርስ በእርስ ግጭትና ብጥብጥ ለመዝፈቅ ሌት ተቀን ይሰራል። ለዚህ እኩይ አላማው ስኬት እንደ ግብጽ ካሉ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል። ከዜች አገር በዘረፈው ሀብት ከምዕራባውያን ሚዲያዎች፣ ከሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ነኝ ባይ ተቋማትና ከቀድሞ አጋር ፖለቲከኞችና አንቂ ተብየዎች ጋርም የሰመረ ሊባል የሚችል ግንኙነት ፈጥሯል።

ይህ የጥፋት ዕቅዱ የማይሳካ ከሆነም ፕላን ቢ(ው)ላይ አበክሮ መስራቱን ተያይዞታል። በመቶ ሺህዎች ልዩ ኃይል እያሰለጠነና እያስታጠቀ ሲሆን በክልሉ ያለውን ሚሊሻም እንደ አዲስ ማደራጀቱንና ማስታጠቁን ገፍቶበታል። ከዚህ ጀርባ ደግሞ የሰሜን ዕዝን በቀላሉ እንዴት እንደሚያጠቃና በአዲስ አበባና በአስመራ የመንግስት ለውጥ እንደሚያደርግ በአረጠ ዘግቶ ያሴራል።

ሕወሓት ፕላን ኤ(ው) የትም እንደማያደርሰውና የፈለገውን ውጤት እንደማያመጣለት ሲረዳ ፕላን ቢ(ው)ን ከመደርደሪያው ሳበ። በሰሜን ዕዝ ላይ ታሪክም ትውልድም ይቅር የማይለውንና የማይረሳውን ክህደትና ጭፍጨፋ ፈጸመ። ሰራዊቱንና አገሪቱን ውድ ዋጋ ቢያስከፍልም እኩይ አላማው ቅዠት ሆኖ ቀረ። የቆሰለ አውሬ ሆኖ የቀረው ሕወሓት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦልም ቢሆን እገባለሁ በማለት በሕዝባዊ ማዕበል ጦርነት ከፈተ። በዚህም በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ትግራዋይን ማገደ፤ በአማራና በአፋር ክልሎች ኀልቆ መሳፍርት የሌላቸውን ግፎች፣ ውድመቶችና ዘረፋዎች ፈጽሞም ቢሆን ድባቅ ተመቶ ቢመለስም ዛሬም ለሌላ ዙር ጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ይገኛል። እንግዲህ ይሄን እፉኝት ለአገዛዝ ያበቃውን ቀን ነው ዛሬም በካሌንደር ዘግተን “እያከበርን” ያለነው። እንደ ዓድዋ እንደ ሚያዝያ 27ቱ የአርበኞች/ የድል በዓል። በተለይ ባለፉት አራት አመታት እንደ አገርም ሆነ ዜጋ የተፈጸመብንን ግፍ ስናስብ ዛሬም የግንቦት 20 መከበር ያማል። ያሳዝናል።

በልጆቹ አጥንትና ደም ተረማምዶ ለስልጣን የበቃበትን ሕዝብ ልጆች ዛሬም ከጉያው እየነጠቀ የሚማግድ በላዔ ሰብዕ፤ በአውራጃና በጎጥ የሚከፋፍል፣ ወላጅና ልጅ፣ ባልና ሚስትን በጥርጣሬ የሚያተያይ፤ የሚያፍን፣ የሚያግትና የቁም እስረኛ የሚያደርግ ነጻ አውጭ አስኳል የሆነበት ድርጅት በምን ተጠየቅና አመክንዮ ነው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን እኩልነት የሚያረጋግጠው? በእርግጥ የይስሙላና በእሱ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አስመሳይ እኩልነት አልነበረም ማለት አይደለም። በመናጆዎቹ በእነ ደኢህዴግ፣ ብአዴን፣ ኦህዴድና በአጋር ፓርቲዎች መካከልና እኩልነትንና ውስጠ ድርጅታዊ ዴሞክራሲና ነጻነትን ሳያረጋግጥ በየት አልፎ ነው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን እኩልነት አረጋግጫለሁ የሚለው !?

ሌላው መመጻደቂያው በግንቦት 20 አገሪቱ ህግ መንግስታዊ፣ ፌደራላዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሪፐብሊካዊ በሆነ ስርአት እንድትመራ ጥርጊያውን ማመቻቸት ተችሏል የሚለው ነው። በቀደሙት 27 የግፍ አመታት ሕገ መንግስቱ ምሰሶ ያደረጋቸው የብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች መብት፣ የሕዝቡ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት መሆኑን፣ የክልሎችን ራስን የማስተዳደር ስልጣን፣ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶችን፣ ወዘተረፈ የሚደነግጉ ድንጋጌዎቹም ሆነ ሌሎች አንቀጾች የኢህአዴግ አዛዥና ናዛዥ የነበረው ትህነግ በአደባባይ ሲጥሳቸው ስለነበር፤ “ሕገ መንግስት የታተመበትን ወረቀት ያህል እንኳ ዋጋ አጣ፤” እስከማለት ተደርሶ ነበር።

በአምስቱም የይስሟላ ምርጫዎች ኮሮጆ በመገልበጥ፣ በማጭበርበርና በአፈ ሙዝ የሕዝቡ ድምጽ በጠራራ በመዘረፉ የሕዝቡን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት በተደጋጋሚ በመጣስ ሲከሰስ መኖሩ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ሌላው በአገሪቱ ታሪክ ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚል መንግስት በገዛ ዜጋው ላይ ዘግናኝና ተቋማዊ በሆነ አሰራር የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶችን እየረገጠ፣ እየጣሰና እየገፈፈ ከፍ ሲልም ሲገድል፣ ዘቅዝቆ ሲገርፍ፣ ጥፍር ሲነቅል፣ ወሲባዊ ጥቃት ሲፈፅምና ሲያንኮላሽ የነበረ ቡድን ስለ ሕገ መንግስትና ሕገ መንግስታዊነት የማውራት ሕጋዊም ሞራላዊም ልዕልና የለውም።

ግንቦት 20 የራስን አስተዳደር በራስ የመወሰን መብት፣ እኩል የመልማት እድል የፈጠረ እና ሁሉም ክልሎች በአገራዊ ጉዳይ ላይ እኩል እንዲወስኑ ያስቻለ ስለ መሆኑን ተደጋግሞ ይነገራል። ሆኖም እኔ አውቅላችኋለሁ እያለ የሞግዚት አስተዳደር በአምሳሉ አቁሞ፤ ክልሎች መሪያቸውን የመምረጥ መብት የገፈፈና በጀታቸውንና እንዳሻው ሲሸነሽን የኖረ አሰራርና አደረጃጀት በነበረበት አግባብ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አጎናጽፏል ቢባል ከልግጫ ያለፈ ትርጉም አይኖረውም። ለዚህ ነው አገዛዙ ፌደራላዊም፣ ዴሞክራሲያዊም፣ ሪፐብሊክም አልነበረም የሚል የሰላ ትችት የሚሰነዘርበት። ለውጡ ካበተ ጀምሮ ግንቦት 20 ይከበር አይከበር የሚለው ሙግትና እሰጥ አገባ ገፍቶ የመጣው። ወንድም ወንድሙን ገድሎ ሥልጣን የያዘበት፤ ሌላ አምባገነን በመንበሩ የተተካበት ሆኖ እንዴት የድል በዓል ይሆናል የሚል ክርክር የተነሳበት፤ መስከረም 2 በግንቦት 20 ተተካ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ እስከ ማለት የተደረሰበት። ለዚህ ነው ዶሴው ይዘጋ፤ የመውጫ ስትራቴጂ እንትለም የምለው።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !**

**አሜን።**

# ወቅታዊ

# «የትግራይ ህዝብ ከዚህ መከራ መውጣት ይፈልጋል፣ ይህንንም ለማድረግ መላው ኢትዮጵያዊ ከጎኑ ሊቆም ይገባል»

- አቶ ብርሃነ ተስፋይ
የትህዴን አባል

አሥመረት ብሥራት

ሕወሓት በትግራይ ህዝብ ስም የተቋቋመ፣ ነገር ግን በስሙ እየነገደ ያለ፣ በትግራይ ህዝብ ላይ በርካታ በደሎችና ግፎችን ሲፈጽም የኖረ ድርጅት ስለመሆኑ የትግራይ ህዝብ ራሱ ምስክር ነው። ይህ ቡድን ግማሽ ምዕተ አመት ለሚሆን ጊዜ አንዴ በነጻ አውጭ ስም፤ ሌላ ጊዜ በመንግስትነት ቆይታው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎችን በጅምላ ጨፍጭፏል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለስደት ዳርጓል፤ የትግራይንም ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ለመነጠል ብዙ ተግባራትን ፈጽሟል። በተለይ ቡድኑ የሃሳብ ነፃነትን በመግፈፍ እና ከራሱና ከራሱ ወዳጆች ውጭ ሌሎች ዜጎችን በማፈን ለብዙ ስቃይና መከራ ሲዳርግ ኖሯል።

ሆኖም ይህንን የአፈና ቡድን በመቃወም እስከ ትጥቅ ትግል ድረስ በመሄድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ አልጠፉም። በዚህ መልኩ ሕወሓትን ሲታገሉ ከኖሩና በመታገል ላይ ከሚገኙ ቡድኖች ውስጥ አንዱ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ትህዴን/ ነው።

እኛም በዛሬው የወቅታዊ አምድ ዝግጅታችን በሕወሓት ሃይሎች ለ13 አመታት ታስረው የነበሩና ከለውጡ በኋላ ከእስር የተለቀቁ፣ አሁንም ከትህዴን ጋር በመሆን ሕወሓትን በመፋለም ላይ ከሚገኙት አቶ ብርሃነ ተስፋይ ጋር በወቅታዊ የአገራችን ሁኔታና በተለይ ሕወሓት እየፈፀመ ስላለው ግፍና መከራ ዙሪያ ቃለምልልስ አድርገናል፤ መልካም ቆይታ።

**አዲሰ ዘመን፤ እርስዎ ቀደም ባለው ጊዜ ሕወሓትን የተቃወሙበት ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**አቶ ብርሃነ፤** ከላይ እንደተጠቀሰው ትህዴን የተመሰረተው በ1993 ዓ.ም ነው። ዋናው አላማው ደግሞ የትግራይ ህዝብ ከኢህአዴግ ዘመነ መንግስት ቀድሞ ደርግን ሲዋጋ በኢትዮጵያ ብሎም በትግራይ ሰላም እናመጣለን፤ በኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጎች እኩል የሆነ ሰላምና ዲሞክራሲ እናመጣለን ብሎ ነበር የታገለው። ሆኖም ግን ደርግ ተሸንፎ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ጊዜ አንስቶ የ ሕወሓት አመራሮች አዲስ አበባን ከረገጡ በኋላ የትግራይ ህዝብን አደራ ወደጎን በመተው ራሳቸውን ወደ መጥቀምና ዘመዶቻቸውን ወደ ማደራጀት ነው የገቡት።

ለትግራይ ህዝብ የተገባለትን አደራ ወደጎን ትተው የራሳቸውን ጥቅም ወደ ማሳደድ ስለገቡ በኢትዮጵያ ብሎም በትግራይ ፍትህ እጦት፤ መከራ፤ እስራት፤ መፈናቀል፤ ረሃብ የተለያዩ ችግሮች መምጣት ጀመሩ። እነዚህን ችግሮች ቁጭ ብሎ መመልከት ስለከበደኝ በአፍላው የወጣትነት እድሜ በአስራ ሰባት አመት እድሜዬ ትህዴንን በመቀላቀል ለትግል ወደ በረሀ ወጥቻለሁ።

**አዲስ ዘመን፤ ይህ ትህዴን የተባለው ድርጅት ምን ያህል አባላት ይዞ ይንቀሳቀሳል?**

**አቶ ብርሃነ፤** አንድ ትግል በስንት አባላት ነው የሚከወነው ተብሎ አይጠየቅም፤ ቅድሚያ መነሳት የሚገባው ጉዳይ የትግሉ አላማ ነው። ዋናው የምትታገይበት አላማ ምን ይመስላል? ህዝቡ ይከተለዋል ወይ? ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? ነው እንጂ ቁጥሩ አይታሰብም። ትግል ደግሞ በቁጥር ሳይሆን በአላማ ፅናት ድል የሚነሳበት ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፤ ለአስራ ሶስት አመታት እስር ቤት ነበርኩኝ ብለውኛልና እስር ላይ ከነበሩ ትግሉን በምን መልኩ ያካሂዱት ነበር?**

“ አሁን የትግራይ ህዝብ ዙሪያው ሕወሓት በተባለ ገደል የተከበበበት ሁኔታ ነው ያለው። መንቀሳቀሻ ሜዳ የለውም ”



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

**አቶ ብርሃነ፤** ትግል ስትታገይ በእስርም፤ በበረሃም በሁሉም መልኩ ነው። አሁን ለምሳሌ እኔ እስር ላይ በነበረኩበት ወቅት ትግሌን አላቋረጠኩም ነበር። ይህም ማለት በእስር ቤት የሚወጡ ወጣቶችን በመመልመል ወደ ትህዴን ሄደው እንዲቀላቀሉ በማድረግ፤ በዛ አካባቢ ያሉ መረጃዎች ለድርጅቱ እንዲደርስ በማድረግ በእስር ቤት ሆኜ ትግሌን አላቋረጥኩም ነበር። ከወጣሁ በኋላ ደግሞ ከትህዴን ጋር ግንኙነቴ ስላልተቋረጠ ወደ ድርጅቱ ልቀላቀል ችያለሁ።

**አዲስ ዘመን፤ መንግስት የጦርነት ፍላጎት ባይኖረም ሕወሓት ደግሞ ወደ ጦርነት እየገባ ይገኛል፤ ለዚህም የትግራይ ህዝብና የዓለም ማህበረሰብ አቋም ምን ሲሆን ይገባል ይላሉ?**

**አቶ ብርሃነ፤** ሕወሓት እስካለ ድረስ ጦርነት አይቆምም፤ ምክንያቱም ይህ የሽብር ቡድን ያለጦርነት መኖር ስለማይችል ነው። ከጦርነት ወጥቶ አያውቅም። ራሱ ስልጣን ላይ በነበረበት ወቅት እንኳን ጦርነትን አቁሞ አያውቅም። መጋጨት ጠብ መፍጠር መዋጋት በዚህ አይነት አካሄድ ነው መኖር የሚፈልገው። ከዚህ ከወጣ ወይም ወደ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ከመጣ ጥያቄዎች ይመጣበታል። ይህ ቡድን ከበረሃ አንስቶ እስካሁን የትግራይ ህዝብ የሚጠይቀውን ጥያቄ አልመለሰም።

ከትግራይ ህዝብ ብዙ ጥያቄዎች ይቀርቡለታል። ከጥያቄዎቹም መካከል በደርግ ጊዜ በበረሀ የተሰው ታጋዮች እነማን እንደሆኑ? የት ቦታ እንደተሰው ተገልፆ ለትግራይ ህዝብ አልተነገረም። ከዚህ ቀን እስከዚህ ቀን ካልመጡ እንደሞቱ ቁጠሯቸው ከማለት በስተቀር ለቤተሰብ መርዶ የነገረ አንድም አካል የለም። ሌላው ደግሞ ሕወሓት በትጥቅ ትግል በነበረበት ጊዜ የትግራይ መሳፍንት የሚባሉ ብዙ የትግራይ ባለሃብቶችን እያፈነ በሌሊት ይወስድ ነበር፤ እነዚህ ሰዎች ይሙቱ ይኑሩ የሚያውቅ ሰው የለም፤ ቢጠየቅም መልስ የሚሰጥ አካል አልተገኘም። ይህ ዋና የትግራይ ህዝብ ጥያቄ ነው። ለዚህ ጥያቄ ደግሞ ሕወሓት ስልጣን ላይ በነበረ ጊዜ መልስ አልሰጠም። ቤተሰቦቻቸውም እስካሁን በጥበቃ ላይ ናቸው። ስለዚህም ነው የህዝብ ጥያቄዎችን ላለመመለሰ ሲል እርስ በእርስ እያባላ የሚኖረው።

**አዲስ ዘመን፤ የትግራይ ህዝብ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የሚኖር ከሆነ መቃወም አልነበረበትም ወይ? አሁንስ ይሄን ስርአት ከላዩ ላይ ለማንሳት ምን ማድረግ አለበት?**

**አቶ ብርሃነ፤** የትግራይ ህዝብ ለውጥም በይው፤ ተቃውሞም በይው፤ አንድ ጉዞ ለመጀመር የሚያስችል ቦታ ሊኖረው ይገባል። ትንሽ መፈናፈኛ ሜዳ ከሌለ ወዴትም መንቀሳቀስ አይቻልም። ከፊትም ከኋላም ዙሪያው ገደል ከሆነ እስከምትወድቅ ወይም ገደል ውስጥ እስከምትገባ ድረስ ዝም ብለህ ትቆማለህ። አሁን የትግራይ ህዝብ ዙሪያው ሕወሓት በተባለ ገደል የተከበበበት ሁኔታ ነው ያለው። መንቀሳቀሻ ሜዳ የለውም።

ይህ የሽብር ቡድን እስካልጠፋ ድረስ የትግራይ ህዝብ መንቀሳቀስም፤ መቃወምም፤ መነቃነቅም አይችልም። ይህን ያደረገው ደግሞ ወዶ አይደለም፣ ሳይወድ ነው። አንድ የታሰረ እስረኛ ከታሰረ መቃወም አይችልም። ከተቃወመ ምን እንደሚደርስበት

# ወቅታዊ

ስለሚያውቅ እሱም አይሞከረውም። በትግራይ ውስጥ ሕወሓትን መቃወም ማለት ራስን በፍቃደኝነት ወደ ጉድጓድ መጣል ማለት ነው።

አሁን የትግራይ ህዝብ ኢጋዥ የሚፈልገበት ጊዜ ላይ ነው። ረዳት ያስፈልገዋል። የሚያግዘው ካገኘ ወደ ሰላማዊው መንገድ ሊመጣ ይችላል እንጂ፤ አሁን በታጠረበት፤ በረሃብ በችግር በጦርነት እየተጎሳቆለ ባለበት፤ ትንሽ ውልፍት ካለ እየታሰረ እየተገደለ ባለበት መቃወም አይችልም። አሁን የትግራይ ህዝብ እየተዳደረ ያለው በፌደራል መንግስቱ ሳይሆን በሽፍታ ቡድን በመሆኑ አንድ የታገተ ሰው ምን አፍ ኖሮት ይቃወማል፤ እንኳን መቃወም መናገርም ከባድ ሆኖበታል።

**አዲስ ዘመን፤ ሕወሓት በዚህ ወቅት ሶስተኛው ዙር ጦርነት ጀምሯል እየተባለ ይገኛል፤ የኢትዮጵያ መንግስትም የአፀፋ ምላሽ እንሰጣለን እያለ ነው እዚህ ላይ ያልዎት አስተያየት ምንድነው?**

**አቶ ብርሃነ፤** የኢትዮጵያ መንግስት ሰላሙን አግኝቶ እስከመጨረሻው ፊቱን ወደ ልማት እንዲመልስ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይህን የሽብር ቡድን ማጥፋት ይኖርበታል። ዝም ብሎ ነካክቶ አባሮ መመለስ አይደለም። ይህ ቡድን ቀበሮ ወይም ጅብ አይደለም። መንደር ገብቶ ሲተናኮል ወደ ጫካ የምትመልሰው፤ ይህ የኢትዮጵያ ጠላት ነውና ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስወግዶ ለትግራይ ህዝብ የሚሆን ከሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተስማምቶ የሚኖር ከጎረቤት ጋር ተስማምቶ የሚኖር ክልላዊ መስተዳድር ማስቀመጥ ነው።

እንደዛ ካልሆነ ግን ቡድኑ ትግራይን እንገነጥላለን የሚል አስተሳሰብ ያነሳሉ፤ ፍላጎታቸው ይህ ከነበረ በስልጣን በነበሩ ጊዜ ለምን አላደረጉትም ነበር። ከአዲስ አበባ ተባረው ሲሄዱ ነው መገንጠል የሚታያቸው? የትግራይ ህዝብ አቅም አግኝቶ በቃኝ ያላቸው ጊዜ አንዲት ወረዳ ይዘው ሊነጠሉ ነው ወይስ ሌላ አላማ አላቸው? የፌደራል መንግስት ማድረግ ያለበት እነዚህን አስወጥቶ የትግራይ ህዝብ ሰላም የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል።

ይህ ህዝብ ሰቆቃና ግፍ በዝቶበት የሚቆረቆርለት ወገን አጥቶ ነገ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም እስኪል ድረስ ዝም ማለት አይገባም። ዛሬ እየተራበ ዛሬ እየሞተ ዝም የሚል የፌደራል መንግስት ካለ ነገ የኢትዮጵያ አካል አይደለንም የሚል ነገር እንዳይመጣ ስጋቴ ነው። ለዚህም ዛሬ ወገኔ ነው የራሴ ዜጋ ነው በማለት ከገባበት ችግር ማስወጣት የግድ ነው የምለው። እርዳታ መላክ ብቻ ሳይሆን ከችግር አውጥተህ የትግራይ ህዝብ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ወንድሙ ጋር በሰላም እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፤ የሕወሓት መሪዎች ለመጨረሻው ምእራፍ ጦርነት ተዘጋጅተናል እያሉ በየመገናኛ ብዙሃኖቻቸው ሲናገሩ ይሰማል፤ ይህ ነገር እንዲያበቃ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ ብርሃነ፤** እነዚህ እኩይ ሃይሎች መሪ ያላቸው እራሱ አይመስለኝም፤ ማን እንደሚመራ አይታወቅም፤ አንዱ በዚህ መጥቶ እኔ ነኝ መሪ ሌላው ደግሞ እኔ ነኝ ይላል። የመጨረሻ የመጥፊያ ካርዳቸውን ስለቀረጡ አምና ተሸውዶ የነበረው ህዝብ ነቅቷል። አምና ፀሎት አድርገን ያመጣናቸውን ሕወሓቶች ተራግመን ማጥፋት አቃተን በማለት ህዝቡ ምሬት ላይ ነው።

አሁን ላይ አንድም በፍቃዱ ጥይት የሚተኩስ ወጣት የለም። ወጣቱ መች  ጦርነቱ ተጀምሮ እጅ እንሰጣለን እያለ ነው። የትግራይ ህዝብ በዚህ ወቅት መቼ ነው ከዚህ ሰቆቃ የምንገላገለው እያለ ይጠብቃል። የተለያዩ መረጃዎችን እናገኛለን። አሁን ጫን ያለ ጦርነት ቢካሄድ ዋናዎቹ  እጅ ይሰጣሉ ወይም ራሳቸውን ያጠፋሉ።

**አዲስ ዘመን፤ ለህዝቡ የሚላከው የእርዳታ እህል ተረጂዎች ጋር አይደርስም፤ ህዝቡ በዚህም እየተጎዳ ነው የሚባል ነገር ይሰማልና ስለዚህ ጉዳይስ ምን አስተያየት አልዎት?**

**አቶ ብርሃነ፤** የእርዳታ እህል ከዚህ ይሄዳል። ልክ እዛ እንደደረሰ በእነሱ መኪና ተገልብጦ ወደ ወፍጮ ቤት ይሄዳል፤ ከዛ በኋላ ለእነሱ ዳቦ መጋገሪያ ቤቶች ይከፋፈላል። ዳቦ ተጋግሮ ማሰልጠኛዎች፤ የወታደር ካምፖች፤ ለካድሬዎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው ደርሶ ካለቀ በኋላ ነው እንግዲህ ከተረፈ ህዝቡ ሊቃመስ የሚችለው።

የትግራይ ህዝብ ሰቆቃ በዚህ መልኩ ነው የሚገለጸው። በስሙ ይነገድበታል እንጂ እንኳን ከችግር የሚያወጣው የሚልስ የሚቀምሰው እርዳታ እጁ ጋር እንዳይደርስ ሆኗል። እንኳን የእርዳታ እህል ሊደርሰው ለነገ ብሎ ያስቀመጠውን እህል እየነጠቁ ይወስዱበታል። ሰው ትርፍ እህል ካለው ሰው ትርፍ ገንዘብ ካለው እየተነጠቀ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ሰው በረሃብ እያለቀ ነው፤ ከህመም ከጦርነትም በላይ በረሃብ የሚፈጀው ህዝብ በጣም በዝቷል። ይህ የእርዳታ እህል በትክክል ህዝቡ ጋር ስለመድረስ ምን ዋስትና አለ።

ህዝቡ እንደማይደርሰው ልናረጋግጥ የቻልነው በተለያዩ የትግራይ ድንበር አቅም ያገኘው ሰው በተለያየ አቅጣጫ እየተመመ ይገኛል። ሰው ሲጠየቅ ረሃቡ እጅግ የከፋ ስለሆነ እየሸሸን ወጣን የሚሉትን ሰምተናል፤ ስለዚህ መንግስት ይሄንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማያዳግም ሁኔታ ይሄን የሽብር ቡድን በማጥፋት ህዝቡን ካለበት ሰቆቃ ማውጣት የግድ ነው።

**አዲስ ዘመን፤ ይህ የሽብር ቡድን የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ ነው ያለው፤ ከፌደራል መንግስቱ ጋርም ሆነ ከጎረቤት አገር ኤርትራ ጋር ትንኮሳ እያካሄደ እንደሆነ ይነገራል፤ ጦርነቱ መጀመሩ ለትግራይ ህዝብም ሆነ ለአገሪቱ ያለው ተፅእኖ ምን ይመስሎታል ?**

**አቶ ብርሃነ፤** ጦርነቱ ዳግም አልተጀመረም። በፊቱኑም አላለቀም ነበር። እየተጓተተ ነው እስካሁን የቆየው። እየተጎተተ ቀን እየረዘመ በሄደ ቁጥር ኢትዮጵያ እየተጎዳች፤ ኑሮው እየተወደደ ኢኮኖሚ እየቀነሰ አገር ወደ ድህነት እየገባች ነው የምትሄደው። ለዚህ መድሀኒቱ የዚህን የሽብር ቡድን እድሜ ማሳጠር ነው። ለዚህ ቡድን ጊዜ እየተሰጠው በሄደ ቁጥር አገሪቱም ወደ ከፋ ችግር እየገባች ትሄዳለች፤ የትግራይ ህዝብም ከቀን ወደ ቀን እያለቀ ይሄዳል። ዛሬ በትግራይ ውስጥ በበሽታ ፤በረሃብ ፤ በጦርነት ስንት ሰው እያለቀ እንደሆነ አይታወቅም። ይህ በቀን ሰው እንደቅጠል እየረገፈ ያለውን የትግራይ ህዝብና ሰቆቃ ለማሳጠር ይህን ሰላም ጠል የሆነ እኩይ ቡድን ይበቃል ማለት የግድ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፤ ሕወሓት ያለጦርነት መኖር ይከብደዋል፤ ሁሉ ነገሩ ከጦርነት ጋር የተያያዘ ነው የሚሉ አካላት አሉ በዚህ ጉዳይ ላይ የእርስዎ ሀሳብ ምንድነው?**

**አቶ ብርሃነ፤** ከላይ እንደገለፅኩልሽ ይህ ቡድን እንዲህ አደርግልሃለሁ ብሎ ቃል ለገባለት የትግራይ ህዝብም ሆነ ለመላው ኢትዮጵያ መመለስ የሚከብደው ብዙ ጥያቄዎች አሉበት። ጥያቄውን ሸሽትም ራሱን በጦርነት ሸፍኖ እየኖረ ይገኛል። በስልጣን በነበረበት ወቅት እንኳን ከጎረቤት አገር ጋር ጦርነት ላይ ነበር፤ ያ ሲያበቃ ደግሞ ህዝቡ በሃይማኖት እርስ በእርሱ እንዲጣላ ሲሞክር ነበር፤ የሃይማኖት ጦርነት አላዋጣ ሲለው በኳሱም ሆነ በሌላ ሰበብ የአካባቢያዊ ግጭቶች እንዲፈጠሩ ሳይታክት ሲሰራ ኖሯል። ሰው በኳስ ምክንያት በድንጋይ ከመወራወር አልፎ ወደ ጥይት መተኳኮስ ሊደርስ ትንሽ ነበር የቀረው። ስለዚህ ይህ ቡድን በፈረቃ ህዝብን ከማፋጀት የበለጠ ስራ የሚባል መልካም ነገር ሳይኖረው ይሄው እስከዛሬ ድረስ አለ።

**አዲስ ዘመን፤ የትግራይ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ መገለጫ ያለው፤ የከበረ ባህልና እሴት ባለቤት የሆነ ህዝብ ነው፤ የሕወሓት ቡድን በዚህ ልክ ጠምዝዞ የፍላጎቱ ማስፈፀሚያ ሲያደርገው የቻለበት ምክንያት ምንድነው?**

**አቶ ብርሃነ፤** ሁሉም ነገር ስርአት አለው። እንኳን ሰው እንስሳት እንኳን የሚመሩበት ስርአት አላቸው። ግን ስርአቱ ተጠብቆ እንዲቆይ መሪ ያስፈልገዋል። ሁሉም ነገር የሚበላሸው ደግሞ በመሪ የተነሳ ነው። የትግራይ ህዝብም መጥፎ የሆነ አመራር ስላለው እየተታለለ ወዳልሆነ ሁኔታ ይገባል እንጂ የራሱ እሴት ባህል የተለየ ማንነት ያለው ህዝብ ነው።

ይህ ብልሹ አስተሳሰብ ያለው ቡድን ደግሞ ህዝቡ እንዳይታይ፣ ማንነቱ እንዲደበቅ፤ ከሌሎች ወንድም ብሔሮች ጋር ተስማምቶ እንዳይኖር አድርገውታል። በእነሱ የጠለሸ ስራ የህዝቡ ስም ጠቁሯል።

**አዲስ ዘመን፤ ሕወሓት ወጣቶችን በግዳጅ ወደ ጦርነት እያስገባ ያለበት ሁኔታ አለ። ወጣቶች ይህ እንዳይሆን ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?**



**አቶ ብርሃነ፤** አሁን ትግራይ ውስጥ ዋና ነቀርሳ ሆነው ያሉ የበታች ካድሬዎች አሉ። የቀበሌ፤ የወረዳና የዞን አስተዳደሮች ከሕወሓት የበላይ አመራሮች በበለጠ የትግራይ ህዝብ ውስጥ ተሰግስገው ህዝቡን እያስጨረሱ ያሉ ናቸው። ወጣቱንም በሃይል አስገደደው ወደ ጦርነት እንዲሄድ የሚያደርጉት ከህዝቡ ጋር በቅርበት ያሉት እነዚህ የበታች ሀላፊዎች ናቸው። የትግራይ ወጣት ወደ ጦርነት እየገባ ያለው በሃይል ነው እንጂ ወዶ አይደለም። ከዚህ አፋኝ ስርአት ማምለጥ የቻሉት በተለያየ አቅጣጫ ወደ እናት አገሩ እየገባ ነው ያለው። በጦርነቱ ታጣቂ የነበረ፤ ሲቪል የነበረ፤ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ሲሰራ የነበረ እና ሌላው ማህበረሰብ ጦርነቱን ጠልቶ አካባቢውን እየጣለ እየመጣ ይገኛል።

ቀደም ሲል ይሄን ያህል የትግራይ ወጣት ተፈናቅሎ አያውቅም ነበር። አሁን ይህን በግዳጅ ወደጦርነት መማገድን በመሸሸ የትግራይ ወጣት ጥሏቸው እየመጣ ነው ያለው። ይህ የሆነበት ምክንያትም የጦርነትን ውጤት በአግባቡ ስላየው ነው። አሁን ላይ በፍቃዱ ወደ ጦርነት የሄደ ወጣት የማይኖር መሆኑን እገምታለሁ።

**አዲስ ዘመን፤ በሕወሓት ቡድን ከአርባ አመት በላይ ህዝብን ከህዝብ የመከፋፈል ስራ ሲሰራ ቆይቷል። የትግራይ ህዝብም ቢሆን ከጎረቤቶቹ ከአፋር ከአማራ ጋር ጠበኛ እንዲሆንም አድርገውታል፣ ይህ አስተሳሰብ መነሻው ከየት ነው ይላሉ?**

**አቶ ብርሃነ፤** የዚህ አስተሳብ መነሻ ከአመጣጣቸው ላይ ነው። ይሄን ስልሽ መጀመሪያ ወያኔ ሲመሰረት በአንድ አካባቢ በትንሹ በጠባብ ሁኔታ ነበር። ይህ አስተሳሰባቸው አድጎ ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ እርስ በእርስ መሳሳብ፤ የየት አካባቢ ተወላጅ ነው ብለው በመጠያየቅ በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ራስን ማስቀመጥ እንጂ ሰፋ ያለ አመለካከት አልበራቸውም። ስለዚህ ከጅምራቸው የተለማመዱት አንደአገር አድጎ ብሔርን ከብሔር ሊከፋፈል በቅቷል።

**አዲስ ዘመን፤ ሕወሓት በአሁኑ ወቅት በትግራይ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና መከራ በምን መልኩ ይገለፃል?**

**አቶ ብርሃነ፤** አሁን በትግራይ ውስጥ ያለው መከራ የሚታወቅና የሚታይ ነው። ምንም ምግብ የለም፤ መድሃኒት የለም፤ ሰው ወደ ልማት ወደ ስራ ሊገባ አልቻለም። ትምህርት ከተቋረጠ ሶስት አመታት ሊሆኑት ነው። ብዙ ወጣቶች ዳግም ወደመሀይምነት እየተጓዙ ነው። አዳዲሰ ትምህርት ቤት መግባት የነበረባቸው ህፃናት ቤት ውለዋል። ህዝብ እንደልቡ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ መንገድ መስራት አልቻለም። በተለያየ የአለማችን ክፍል የነበሩ የትግራይ ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋር መገናኘት አልቻሉም። በአጋጣሚ ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይ ሄደው እዛው የቀሩ፤ ከዛም ወደዚህ መጥተው የተለያዩ ቤተሰቦችም በርካታ ናቸው።

የትግራይ ህዝብ በሕወሓት ምክንያት ተቆጥሮ የማያልቅ ግፍና መከራ እያደረሰ ስለሆነ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የዓለም ማህበረሰብ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶት ይህ መከራ በአጭሩ እንዲያልቅ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፤ ሕወሓት የተንኳሽነት ባህሪውም በአገር ውስጥም ሆነ ከጎረቤቶች ጋር ያሳያል፣ ፍላጎቱ ምንድነው ይላሉ?**

**አቶ ብርሃነ፤** የሕወሓት ፍላጎት ሁሉም የትግራይ ህዝብ እንዲቆስል እንዲደማ ነው። በየቤቱ ሰው እንዲሞት ሀዘን ሁሉንም እንዲያዳረሰ ነው። ይህንንም የሚያደርጉት እነሱ እንዳበቃላቸው ያውቃሉ። የነሱ ልጆች ግን ውጭ ነው ያሉት። ውጭ ሆነው እየተማሩ የዓለምን አስተሳሰብ ለመቀየርና የነሱን እድሜ ለማራዘም እየሰሩ ይገኛሉ። እነዚህኞቹ ከወደቁ ዳግም ለማንሰራራት እንዲመቻቸው ትናንት ተመችቷችኋል ቆስላችኋል በማለት ለማነሳሳት እንዲመቻቸው መደላድል ለመስራት ነው።

**አዲሰ ዘመን፤ ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለ እድሉን ልስጥዎት?**

**አቶ ብርሃነ፤** ትግራይ ውስጥ ላገጠመው ችግር በአቅሙ መፍትሄ ለመስጠት ድርጅታችን ትህዴን ትግል ላይ ይገኛል። በዚህ ትግልም የትግራይ ህዝብ ከጎናችን እንዲሰለፍ ጥሪ እናቀርባለን። የትግራይ ህዝብ ከኢትዮጵያ መነጠል እንደማይፈልግ የኢትዮጵያ ህዝብ ተረድቶ ሁለቱን ወንድማማች ህዝቦች ለመነጠል የተዘጋጀውን ቡድን ለማጥፋት በሚደረግ ጥረት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን ቢቆም መልካም ነው። የትግራይ ህዝብም ከሞተው ሕወሓት ጋር አብሮ መሞት ሳይሆን ይህን የሞተ ቡድን በማጥፋት ከተቀረው ወንድም ህዝብ ጋር አብሮ እንዲኖር ማድረግ አለበት። ትህዴን በትግራይ ዙሪያ የድንበር ከተሞች ስላሉ መምጣትና ትግሉን መቀላቀል የፈለገ ወደትግሉ መቀላቀል ይችላል።

**አዲስ ዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ብርሃነ፤** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## አገራዊ የማምረት አቅምን ማጎልበት - ለኢንዱስትሪ ዘርፉ ዕድገት

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለማሸጋገር ስትሰራ ቆይታለች። ለዚህም የግሉ ዘርፍ በኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚደርገው ኢንቨስትመንት እንዳለ ሆኖ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመሳብ እየሰራች ትገኛለች። የዘርፉን ተግዳሮቶች ለመፍታት ርብርብ በማድረግም በተለይ ለኢንቨስትመንት በሚውል መሬት አቅርቦትና መሰረተ ልማት ላይ ተሰርቷል።

በሀገሪቱ ተገንብተው ወደ ስራ የገቡ በርካታ ግዙፍ የኢንዱስትሪ ፓርኮችንም ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል። የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ በውጭ ባለሀብቶች በኩል ከቦታ፣ ከመሰረተ ልማት ጋር ተይይዞ ይቀርቡ የነበሩ ጥያቄዎችን መፍታት ችለዋል። ይህም ዘርፉን የሚቀላቀሉ ግዙፍ ታዋቂ የውጭ ሀገር ኩባንያዎችን ጨምሮ ከፍተኛ መጠን ያለው ካፒታል የመደቡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ገብተው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ኩባንያዎቹ ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ከጀመሩም ቆይተዋል። ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት በኩልም የራሳቸውን ሚና እየተጫወቱ ናቸው።

እንዲያም ሆኖ ዘርፉ ዛሬም በርካታ ጥያቄዎች እየተነሱበት ይገኛል። በዓይነትም ሆነ በብዛት በርካታ የሆኑት የዘርፉ ችግሮች፤ የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና በአጠቃላይ የሕዝቡን የተቀናጀ ጥረት የሚፈልጉ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ይገለጻል። ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ብዙ ሙከራዎች ተደርገው የማይናቁ ውጤቶች ቢመዘገቡም፣ ከአገሪቱ አቅምና ከችግሮቹ ስፋት አንፃር ግን መፍትሄዎቹ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አስገኝተዋል ብሎ መናገር አይቻልም።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዘጋጅነት በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልል ከተሞች እየተካሄደ የሚገኘው የ ‹‹ስለ ኢትዮጵያ›› መድረክ አካል የሆነውና የኢንዱስትሪው ዘርፍ ተዋንያን፣ የመንግሥት የስራ ሃላፊዎች በተገኙበት በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ያተኮረ የውይይት መርሃ ግብር ሰሞኑን በድሬዳዋ ከተማ በተካሄደበት ወቅትም የዘርፉ መልካም አጋጣሚዎች፣ ችግሮች ተመላክተው ሰፊ ውይይትም ተደርጎ መፍትሄዎች ተጠቁመዋል።

በውይይቱ ላይ የአምራች ዘርፉ እድሎችንና የመንግሥትን ትኩረት በተመለከተ ገለፃ ያቀረቡት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፣ የኢትዮጵያን የሕዝብ ብዛት፣ የአምራች ኃይል አቅም፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ሕጋዊ ማዕቀፎችና ለዘርፉ እድገት አወንታዊ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችንና አስቻይ ሁኔታዎችን በመጥቀስ አገሪቱ በኢንዱስትሪ ዘርፉ ግዙፍ አቅም እንዳላት አስረድተዋል። በዘርፉ ከተፈጠረው የሥራ እድል ባሻገር በኢንዱስትሪ ፓርኮች አማካኝነት ለአርሶ አደሮች የገበያ ትስስር መፍጠር መቻሉንም ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ጥቅል አገራዊ ምርት የስድስት ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ አለው፤ ይህን ድርሻ ወደ 17 ነጥብ 2 በመቶ ለማሳደግ እየተሰራ ነው። ይህን እቅድ ማሳካት ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ የውጭ ምንዛሪ እጥረትንም ለማቃለል አይነተኛ መፍትሄ ነው።

‹‹አሁን ያለው የኢንዱስትሪዎች የምርታማነት አቅም 50 በመቶ ነው፤ በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠረው የማምረት አቅም ማነስ ምርት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይቀርብ አድርጓል። በቀጣይ የአምራቹን አቅም ወደ 85 በመቶ ለማድረስ ውጥን ተይዟል›› ሲሉ ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

አገሪቷ ያላትን ትልቅ የዘርፉን እምቅ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ይቻል ዘንድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር በቅርቡ የ ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ መጀመሩን ገልጸዋል። የዚህ ንቅናቄ ምሰሶዎችም ባለድርሻ አካላትን ማሣተፍ፣ ዘርፉን በጥናትና ምርምር መደገፍ፣ ለዘርፉ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ እና የሀገር በቀል ምርቶችንና አመራረትን ማሳደግ መሆናቸውን አብራርተዋል። የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግርን ለመፍታት የመጀመሪያውና መሠረታዊው መፍትሄ የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ እንደሆነ ያስረዱት አቶ መላኩ፣ ከዚህ አንፃር ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ተናግረዋል።

አገሪቱ ያላትን የኢንዱስትሪ አቅም ገቢራዊ ለማድረግ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ተወዳዳሪ ማድረግ ይገባል። ‹‹የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› እንዲሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍና ተወዳዳሪ የማድረግ ጉዳይ በምጣኔ ሀብት ትብብርና በእርዳታ ስም የሚደረግን የሀብታም ሀገራትንና ተቋሞቻቸውን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት ሉዓላዊነትን እስከማስከበር ድረስ የዘለቀ ትርጉምና ፋይዳ አለው።




በመድረኩ የኢንዱስትሪ ዘርፉን መልካም አጋጣሚዎች፣ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎች በተመለከተ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፤

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አህመድ፣ የግሉ ባለሀብት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ስላለለው ተሳትፎ፣ ስላበረከተው አስተዋፅኦ እና ስላሉበት ችግሮች ማብራሪያ ሰጥተዋል። ለአንድ አገር ዘላቂ እድገት የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ያላቸው ሚና የማይተካ መሆኑን አቶ ጀማል ይጠቅሳሉ፤ የውጭ ባለሀብቶች ለውድድር እና ተሞክሮዎች እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ተናግረው፣ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባም ነው ያስገነዘቡት።

ዋና ስራ አስፈፃሚው መንግሥት ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚያደርገውን ድጋፍ ማሳደግ እንዳለበት ጠቁመው፤ ‹‹የአገር ውስጥ አምራቹ ከውጭ አገራት ግብይት ከሚያገኘው የንግድ ሥራ ያገኛትን የውጭ ምንዛሪ ለተጨማሪ ኢንቨስትመንት የማዋል ፍላጎት አለው። ችግሮች በአንድ ጊዜ አይፈቱም፤ ቢሆንም ግን ለውጭ አገር ባለሀብቶች የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ሊሠጠን ይገባል›› ብለዋል።

አምራች ኢንዱስትሪው ለዘላቂ ልማት ዋነኛ ሞተር ነው ያሉት አቶ ጀማል፤ በዘርፉ ያለውን እምቅ ሀብት ለመጠቀም የባለሀብቱ ችግሮች ተለይተው ሊታወቁና መፍትሄ ሊፈለግላቸው እንደሚገባም አሳስበዋል። የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የአጠቃቀም ፍትሃዊነት መጓደል፣ የሥራ ባህል ደካማነት እንዲሁም ዘርፉን ለማበረታታት የሚወጡ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች በአግባቡ አለመተግበር የዘርፉ ባለሀብቶች ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን አቶ ጀማል አስረድተዋል።

እንደ ዋና ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ አምራች የግል ባለሀብቶችን ይበልጥ ለመደገፍ በግሉ ዘርፍ የሚቀርበውን የውጭ ምንዛሬ በፍትሐዊነት ማከፋፈል ይገባል። በተለያዩ ጊዜያት እንደሚታየው በአገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች እጥረት አለ በሚባልበት ወቅት በዚያው ልክ ደግሞ የቅንጦት ዕቃዎች በብዛት ወደ አገር ውስጥ ይገባሉ። ፋብሪካዎች በመለዋወጫና በግብዓት እጥረት በሚዘጉበት አገር፣ የቅንጦት ዕቃዎች በብዛት መግባታቸው የውጭ ምንዛሬ ድልድል በፍትሐዊነት እንደማይቀርብ ያሳያል።

ደሃ ሀገር ላይ እንደመሆናችን የጥሬ ዕቃ ችግር አለብን፤ በመሆኑም ከፍተኛ የፋይናንስ አቅርቦት ያስፈልገናል። ይህን አይነት ችግር ያለበትን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ መንግሥት ለመደገፍ የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ ቢሆንም በውጭ ምንዛሬ ጉዳይ ላይ ያለውን ችግር ማስተካከል ይገባል›› ብለዋል።

‹‹ሁሉም ችግሮቻችን በአንድ ጊዜ ይፈቱልን አንልም፤ አንጠብቅምም›› ያሉት አቶ ጀማል፤ መንግሥት ከባለሀብቱ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ችግሮቹን መፍታት እንደሚገባውም ተናግረዋል። ‹‹በተለይ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን በፍትሐዊነት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በማቅረብ ዘርፉን ማሳደግ ይገባል›› በማለት ተናግረዋል።

አቶ ጀማል መንግሥት የአገር ውስጥ አምራቾች እንዲበረታቱ ለዓመታት ያከናወነው ስራ በተለያዩ ዘርፎች የግል ባለሀብቱ እንዲጠናከር አቅም መፍጠሩን ተናግረው፣ በሕዝቡም ሆነ በመንግሥት በኩል የአገር ውስጥ ምርት በመጠቀም ረገድ ያሉ ክፍተቶችን ማስተካከል እንደሚገባ ገልጸዋል። ለዚህም ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የተሰኘው ንቅናቄ ትኩረት ተሰጥቶት በትክክል ከተተገበረ ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

‹‹ኢትዮጵያን ከኢንዱስትሪ ውጭ ማሰብ አይቻልም›› ያሉት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ፣ መንግሥት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ ዘርፉን ለማጠናከር በ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የአቅም ማጠናከር ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል። ከመንግሥት ጥረት ባለፈ ባለሀብቱም ተገቢውን የኢንዱስትሪ አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ምርታማነትን ማሳደግ እንዳለበትም ተናግረዋል።

የውጭ ምንዛሪ እጥረቱን በዘላቂነት ለመፍታት በመፍትሄነት ከተለዩ ቁልፍ አማራጮች መካከል የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ አንዱ ነው። የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴም የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግር በዘላቂነት ሊፈታ የሚችለው የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ ሲቻል እንደሆነ አስረድተዋል። መንግሥት የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ቅድሚያ ማግኘት ያለባቸውን ዘርፎች ለይቶ እየሰራ መሆኑን ያብራሩት ሚኒስትሩ፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ግን ያመነጩትን የውጭ ምንዛሬ መጠቀም መብታቸው ነው የሚል አሰራር ፈቅዶ ተግባራዊ አድርጓል ብለዋል። ባለሀብቶች የሚያነሱትን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በቅድሚያ ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንደሚኖርባቸውም ገልጸዋል።

እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፤ የመንግሥት ዋና አላማ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን መደገፍና ማብቃት ነው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌሎች አገራት ኢንቨስትሮች በተሻለ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጽኑ ፍላጎት አለው። የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ አቅም ሲጠናከር መዋዕለ ንዋዩንም መልሶ ለሀገር ለማዋል ይችላል፤ በዚያው ልክም አካባቢውን በመጥቀም የስራ ዕድሎችንም በስፋት ለመፍጠር አቅም ይኖረዋል።

‹‹ከዚህ አንፃር፣ ከአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች ድረስ መንግሥት የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን በማሳደግ እና በልዩነት በተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ ኢትዮጵያውያንን ብቻ እንዲሰሩ በማድረግ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል›› ብለዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ ‹‹የሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ይበልጥ እንዲጠናከር ድጋፍ ይደረግለታል ሲባል ግን ኢንዱስትሪው በሀገር ውስጥ አቅም ብቻ ይሳካል ብሎ ማሰብ አይገባም›› ሲሉ አስገንዝበዋል። ‹‹ምክንያቱም የፋይናንስና የቴክኖሎጂ አቅማችን ገና ውስን በመሆኑ ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅቶ መስራት ያስፈልጋል። በመሆኑም ሁለቱም ተቀናጅተው እንዲሰሩ መደገፋችንን እንቀጥላለን። የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በቅንጅት እንዲሰሩ ማድረግ በተለያዩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጤት ማምጣት ተችሏል›› በማለት ስለሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ቅንጅት ፋይዳ ገልጸዋል።

የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ዘላቂ የቴክኖሎጂ እድገትና የሥራ እድል የሚፈጥር እንዲሆን በሀገር በቀል ኢኮኖሚው ዋነኛ ትኩረት እንደተሰጠው የተናገሩት የገንዘብ ሚኒስትሩ፤ በመንግሥት በኩል መሠረተ ልማትን ለማሟላት፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትን ለማሳደግና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለውን ቢሮክራሲ ለማቅለል የሚረዱ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን አመልክተዋል።

እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመፍታት የመጀመሪያውና መሠረታዊው መፍትሄ ምርትን ማሳደግ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል። የሌሎች አገራት ተሞክሮም የሚያሳየው ይሄንኑ በመሆኑ ምርት ላይ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል። በእኛ ዘንድ ያለው ችግር የፖሊሲ ሳይሆን ያሉትን ፖሊሲዎች በጥራት ያለመፈፀም እና የአመራሩ ቁርጠኝነት ማነስ ነው። በባለሀብቱ በኩል ያለው የማስፈጸም አቅም ማነስ ችግር ዘርፉ የሚጠበቅበትን ያህል እንዳያመርት አድርጎታል። አንድ ባለሀብት ብዙ ገንዘብ አውጥቶ የገነባውን ፋብሪካ የተማረና አቅም ያለው ሠው እንዲመራው ከማድረግ ይልቅ የትምህርት ደረጃው ብቁ ያልሆነን ዘመዱን በማስቀመጥ ወደ ኪሳራና ብክነት ይገባል፤ ይህ መስተካከል አለበት።

በድሬዳዋ ከተማ ስላለው የኢንዱስትሪ ዘርፍ አቅም፣ የዘርፉ ልማትና እንዲሁም የከተማዋ አስተዳደር ስለሚያደርገው ክትትልና ድጋፍ ማብራሪያ የሰጡት የከተማዋ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሃር በበኩላቸው፤ ድሬዳዋ ለኢንቨስትመንት የተመቸች እንዲሁም አመራሩም ባለሀብቱን በቅርበት የሚከታተልና የሚደግፍ እንደሆነ ተናግረዋል።

ከተማዋ ለጅቡቲ ወደብ ቅርብ እንዲሁም ለባቡር ጭነት አገልግሎት የተመቸች መሆኗን ከንቲባው ጠቅሰው፣ ይህም ከተማዋን ለባለሀብቱ ሥራ እጅግ ተመራጭ እንዳደረጋት ይገልጻሉ። በዚህም ምክንያት በቅርብ ዓመታት ውስጥ በርካታ ባለሀብቶች ወደ ከተማዋ በመግባት በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ መሰማራታቸውን ይጠቅሳሉ።

የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ በማድረግ በቅርብ ዓመታት ውስጥ በአምራች ኢንዱስትሪው የውሃ እና የሲሪንጅ ማምረቻ ፋብሪካ፣ ሆስፒታል፣ ሆቴሎች እና ሌሎች ፋብሪካዎች ተገንብተው ሥራ መጀመራቸውን ከንቲባው ገልጸዋል። የከተማው ሕዝብ የሠላሙ ዘብ በመሆን ለባለሀብቱ ኢንቨስትመንት ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋልም ብለዋል።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት በብዙ ርቀት ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ለወቅቱ የሚመጥን ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ የማምረት አቅምን ማጎልበት ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ የመፍትሄ አቅጣጫ ነው።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

## ጎሜ

# ከባህር ዛፍ ፖለቲካ ያልተሳቀቀው ሱፍ ለባሽ

**ሙሉቀን ታደገ**

በባለፈው ሳምንት ዝግጅታችን ወፈፌው ይልቃል አዲሴ እንደዚህ ቀደሙ በሌሊቱ ተነስቶ በሰፈራችን ከሚገኘው ዋርካ ስር ቆሞ «ዋጋ እንዳንከፍል እንደማመጥ!» እያለ ሲጮህ ከአራቱም አቅጣጫ የይልቃል አዲሴን ጩኸት እንደ መጽሐፍ ለማንበብ የተሰባሰቡት የሰፈራችን እና የእድራችን ሰዎች የይልቃል እዲሴን ንግግር በጥሞና እያዳመጡ እያለ አብሿሙ ክንፈ ጉደታ የይልቃ አዲሴን ንግግር ማቋረጡን እና የአብሿሙን የክንፈ ጉደታ ጥያቄ እና የወፈፌውን ይልቃል አዲሴን ምላሽ ለቀጣይ ሳምንት ይዘን እንደምንቀርብ ቃል ገብተን ነበር።

እንደሚታወሰው አብሿሙ ክንፈ ጉደታ የይልቃ አዲሴን ንግግር ያቋረጠው ይልቃል አዲሴ በዋርካው ስር የተሰበሰበውን ሰው «ኧረ ጎበዝ ! አሜሪካ እና መሰል የሰፈራችን እና የእድራችን ታሪካዊ ጠላቶች እኛን ለማባላት እና ለመብላት እየጎነጎኑት ባለው ሴራ እርስ በርስ ተባልተን ሳንጠፋ አሁኑኑ እንደማመጥ። አለበለዚያ ሰፈራችን እና እድራችን «ወደ ነበርነት» መቀየሩ የማይቀር ነው።» እያለ ባለበት ጊዜ ነበር።

አብሿሙ ክንፈ ጉደታ አብሿም የተባለው ከሰፈራችን እና ከእድራችን ሰዎች አስተሳሰብ ትንሽ ወጣ እና ፈጠን ያለ ባህሪ ስላለው እንጂ የእውነት አብሾ መጠጣቱን ከሰፈራችን ይሁን ከእድራችን አባላት አንድም ያረጋገጠ ሰው የለም ። ያም ሆነ ይህ ! አብሿሙ ክንፈ ጉደታ ሁለት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ነበር የወፈፌውን ይልቃል አዲሴ ንግግር ያቋረጠው። የአብሿሙ ክንፈ ጉደታ አንደኛው ጥያቄ የሰፈራችን እና እድራችን ህልውና አደጋ ላይ መውደቅ ዐብይ ምክንያት ለይስሙላ ፊደል ቆጥረናል በሚሉ ፤ ሳያውቁ ራሳቸውን በአዋቂዎች መርከብ ያሳፈሩ አንዳንድ የእድራችን አስተዳዳሪዎች ፣ ተፎካካሪ ሃይሎች ፣ ወግ አሳላጮች እና ጡሩምባ ነፊ ሱፍ ለባሾች ነው። እነኚህ አካላት እንዴት ለሰፈራችን እና ለእድራችን ህልውና ስጋት ሊሆኑ ቻሉ? የሚል ሲሆን ፤ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ እነኚህ አካላት ለምን መደማመጥ ተሳናቸው? የሚል ነው።

አብሿሙ ክንፈ ጉደታ የይልቃል አዲሴን ንግግር ቢያቋርጠውም ይልቃል አዲሴን በአብሿሙ ክንፈ ጉደታ ሳይበሳጭ ፤ ፈገግታ ከፊቱ ላይ ሳይለየው የተጠየቀውን ጥያቄ ለመመለስ ጉሮሮውን እየጠራረገ.....ንግግሩን እንዲህ ሲል ጀመረ ....

እውነት ነው ! ክንፈ ጉደታ ለመጥቀስ እንደሞከረው ለሰፈራችን እና እድራችን ህልውና ሁነኛ ካንሰሮች እና መድሃኒት የሌላቸው በሽታዎች ለይስሙላ ፊደል ቆጥረናል የሚሉ ፤ ሳያውቁ ራሳቸውን በአዋቂዎች መርከብ ያሳፈሩ አንዳንድ የእድራችን አስተዳዳሪዎች ፣ ተፎካካሪ ሃይሎች ፣ ማን እንደሚከፍላቸው የማይታወቁ ወግ አሳላጮች እና ጡሩምባ ነፊ ሱፍ ለባሾች ናቸው። ሁሉም ሱፍ ለባሾች መጥፎ ናቸው ባይባልም አብዛኛዎቹ በሰፈራችን እና በእድራችን የሚገኙ ሱፍ ለባሾች ግን የንጹሃንን ደም የማፍሰስ ዛር የተዋረሳቸው ፤ የእድራችን እንዲሁም የሰፈራችን ታሪካዊ ጠላቶች በሆኑት አሜሪካ እና መሰል ሀገራት ነዋይ የተገዙ የነዋይ ሴሰኞች ናቸው ።

የሰፈራችንን እና የእድራችንን እያንዳንዷን እርምጃ የሚቆጥሩት አሜሪካ እና መሰል የእድራችን እና የሰፈራችን ታሪካዊ ጠላቶች ለይስሙላ ፊደል ቆጥረናል የሚሉ ፤ ሳያውቁ ራሳቸውን በአዋቂዎች መርከብ ያሳፈሩ ሱፍ ለባሾችን በነዋይ ገዝተው እድራችንን እና ሰፈራችንን እንደፈለጉ ማድረግ እንደሚችሉ ከተረዱ በርካታ አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል። ይህን ተከትሎም የጥቁሮች ኩራት እና የነጻነት ተምሳሌት የሆነችውን ሰፈራችንን ሆነ ብለው የስም የማጥፋት ዘመቻ (character assassination) አደረጉባት። በዚህም ሆነ ተብሎ በሚደረግ የስም የማጥፋት ዘመቻ (character assassination) ሰፈራችንን እና እድራችንን ስም ከማጠልሸትም አልፈው እንደ ሰፈር እና እድር የመኖር ህልውናችንንም መፈታተን ከጀመሩ በርካታ ጊዜያት ተቆጥረዋል።

ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ያላቸው ጥላቻ የቆየ መሆኑን ለመረዳት እ.ኤ.አ በ1927 በባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ የተጻፈው እና በከያኒ ደበበ እሸቱ ወደ አማርኛ የተተረጎመው “Abessinien: Die schwarze Gefahr” ወይም «የባሩድ በርሜል» የተሰኘውን መጽሃፍ ማየት በቂ ነው።

> የእድር መሪዎች የሚመሩት እድር ህልውና በጸና መሰረት ላይ እንዲቀመጥ ከፈለጉ በመጀመሪያ ደረጃ እድሩ ሁነኛ ዓላማ ሊኖረው ይገባል። ዓላማውም በመርህ የተገራ እና በመርህ ሊመራ ግድ ነው። መርህ ደግሞ ዓላማን ለማሳካት መራራም ሊሆን ይችላል። የብዙ እድሮች ተሞክሮ ይሄንን በግልጽ የሚያሳይ ነው። መርህ ደግሞ ለአንድ አድር መሪ «ሀሁ» ነው።

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ፤ የባሩድ በርሜል የተሰኘው ጻሃፊው ባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ ይባላል። አስትሪያዊ ሲሆን ፤ ዋነኛ ተግባሩም በሰፈራችን እና በእድራችን መሰብሰቢያ ዋርካ ስር የዲፕሎማሲያዊ ስራ መከወን ነበር ። ይህ ሰው በ1926 ዓ.ም ከዲፕሎማት ሥራው እና ከዲፕሎማቲክ መብቱ ጋር የሚፃረር ተግባር ሲያከናውን በመገኘቱ የእድራችን እና የሰፈራችን መሪዎች ከመሰብሰቢያ ዋርካ ስር በብርሃን ፍጥነት በማባረር ወደ ሀገሩ መለሱት። ቂም አርግዞ ወደሀገሩ የተባረረው ዲፕሎማትም መርዝ ያዘለ መጽሃፍ ጻፈ።

አሜሪካ እና መሰል የእድራችን እና የሰፈራችን ታሪካዊ ጠላቶች ሰፈራችንን እና እድራችንን ለማጥፋት ካላቸው ጉጉት የተነሳ በ1927 ዓ.ም በባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ የተጻፈውን መጽሃፍ በ34 የአውሮፓ ቋንቋዎች ተተርጉሞ እንዲጻፍ አደረጉ።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተተረጎመውን ያነበቡ ለይስሙላ ፊደል ቆጥረናል የሚሉ ፤ ሳያውቁ ራሳቸውን በአዋቂዎች መርከብ ያሳፈሩ አንዳንድ የእድራችን አስተዳዳሪዎች ፣ ተፎካካሪ ሃይሎች ፣ ማን እንደሚከፍላቸው የማይታወቁ ወግ አሳላጮች እና ጡሩምባ ነፊ ሱፍ ለባሾች ፤ የባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ የጠላች ንግግሮች ፖለቲካ ማኒፌስቶአቸው አድርገውት አረፉ።

ከእነኝህ መካከል አንዱ የሆነው እና ሰፈራችንን እና እድራችንን ለሶስት አስርት ዓመታት የመራው በአይተ ጭሬ ልድፋው የሚመራው ሱፍ ለባሽ ቡድን በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ነው ።

ለይስሙላ ፊደል ቆጥረናል የሚሉ ፤ ሳያውቁ ራሳቸውን በአዋቂዎች መርከብ ያሳፈሩ አንዳንድ የእድራችን አስተዳዳሪዎች ፣ ተፎካከሪ ሃይሎች ፣ ማን እንደሚከፍላቸው የማይታወቁ ወግ አሳላጮች እና ጡርምባ ነፊ ሱፍ ለባሾች የምዕራባውያን የሴራ ማሳለጫ ፈረስ ከሆነው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እየተባለ ከሚጠራው ድርጅት ጋር በመተባበር ሰፈራችን እና እድራችንን ለማፍረስ የሚሮጡት የጥፋት ሩጫ በሰፈራችን እና እድራችን ላይ እያሳደሩት ያለውን ተፅዕኖ ለመረዳት በባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ የተጻፈውን መጽሃፍ በወፍ በረር ማየቱ ተገቢ ነው ። ስለሆነም ስለመጽሃፉ ትንሽ ልበላችሁ! አለና .. ይልቃል አዲሴ ለአፍታ ንግግሩን ገታ ካደረገ በኋላ ንግግሩን እንዲህ ሲል ቀጠለ....

መጽሃፉ ምዕራፍ አንድ ላይ “በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደው ምንድን ነው? ” የሚል ርዕስ የያዘ ነው ። በዚህ ርዕስ ተነስቶ በሀገሪቱ ስለሚካሄዱ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ይዳስሳል። መጽሃፉ ስለ ሀገሪቱ መልክዓ ምድራዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኩነት ያትታል ፣ ቅኝ ተገዥ ከሆነው ከሌላው ዓለም ህዝብ የሚያገኙትን ክብርና ታዛዥነት ኢትዮጵያ ውስጥ ማጣታቸውን ሳይደብቅ ይነግረናል። ይህንን የኢትዮጵያውያን ኩራት ማኮስመን ካልተቻለ እና በቸልተኝነት ከታለፈ ወደ ሌሎቹ የአፍሪካ ሀገሮች ተሸጋግሮ ዋጋ ያስከፍለናል ሲል ይመክራል።

የኢትዮጵያውያን ኩራት እና የራሳቸውን ችግር በራሳቸው ለመፍታት የሚያደርጉትን ጥረት ማኮስመን እንደሚገባ ለአውሮፓውያን ይመክራል። ኢትዮጵያውያን በተለይም አንደኛው ብሔር ለውጭ ሃይሎች ያላቸው ጥላቻ ለሁሉም የውጭ መንግሥታትና ዜጎች አሳሳቢ በመሆኑ ፤ ይህንን ብሄርን ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር በማጋጨት ኢትዮጵያን እንዳትነሳ አድርጎ ማጥፋት እንደሚቻል ይገልጻል።

በ1968 ዓ.ም በእጅ የጻፈው አይተ ጭሬ ልድፋው ማኒፌስቶው መነሻው የባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ መጽሃፍ መሆኑን በማያወላዳ መልኩ መገንዘብ ይቻላል ። የእነ አይተ ጭሬ ልድፋው ቡድን ማኒፌስቶን ከባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ መጽሃፍ ጋር መስመር በመስመር ብታስተያዩት ለሶስት አስርት ዓመታት ሰፈራችን እና እድራችን ሲያስተዳድረው የቆየው ሱፍ ለባሽ ከፍጥረቱ ጀምሮ የምዕራባውያን የጥፋት አሽከር መሆኑን በቀላሉ እንድንገነዘብ ያስችለናል። አሁን ላይ የሚታዩ አንዳንድ በብሄር ጥላቻ የሰከሩ ሱፍ ለባሾችም የፖለቲካ እውቀት መነሻው የባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ መጽሃፍ መሆኑን በማያወላዳ መልኩ ያስገነዝበናል።

የዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት “ጥቁር መጽሐፍ የኢትዮጵያውያን የጥቃት ስንዘራ” የሚል ርዕስ ያዘለ ነው። በዚህም ነጮች ኢትዮጵያ ውስጥ ሲመጡ የሚገጥማቸውን መከራና ሰቆቃ ይዘረዝራል። ለውጭው ዓለምም ለጥቁር አሜሪካውያን ሳይቀር ኢትዮጵያ ማለት ለእንግዳ ክብር የማትሰጥ የምድር ሲዖል እንደሆነች አድርጎ ያለግብሯ ግብር እና ያለታሪኳ ታሪክ ለመስጠት ይሞክራል።

ይህን የኢትዮጵያን ክብር ለማውረድ ሲጣጣር የሚመለከት ማንኛም ሰው የአሸባሪው አይተ ጭሬ ልድፋው እና ግብረ አበሮቹ ሱፍ ለባሾች በሰፈራችን እና እድራችን ታሪክ የ100 ዓመት ነው ብለው ታሪካችንን ለማሳነስ የጀመሩት እሩጫ መነሻው የባሮን ሮማን ፕሮቻዝካ ጹህፍ መሆኑን ለመረዳት ያስችላል ። ለመጀመሪያው ጥያቄህ ይህን ያህል ካብራራሁ ጊዜ ስሌለን ለሁለተኛው ጥያቄህ መልስ ብሰጥ ይሻላል በማለት የሁለተኛውን ጥያቄ ምን እንደነበር ለማስታወስ በብጫቂ ወረቀት ላይ የጻፋትን ማስታወሻ አነበበ።

ካልተሳሳትኩ ክንፈ ጉደታ ሁለተኛው ጥያቄህ ሰፈራችን እና እድራችን በብዙ ችግሮች ተተብትበው ተይዘው መላወሻ ባጡበት ሰዓት ሰፈራችንን እና እድራችን የሚመሩት እና ተፎካካሪዎቻቸው እንዲሁም ወግ አሳላጭ እና ጡሩምባ ነፊ ሱፍ ለባሾች እንዴት መደማመጥ ተሳናቸው ? የሚል ነው .. ብሎ ፤ ይልቃል አዲሴ አብሿሙን ክንፈ ጉደታ ተመለከተ ። አብሿሙ ክንፈ ጉደታ በአወንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ።

ይልቃል አዲሴ ንግግሩን ቀጠለ.... አንዳንዴ ቆም ብየ ሳስብ ሱፍ የተባለ ልብስ ሰዎች መደማመጥ እንዳይችሉ እና ከራሳቸው ውጭ ማንንም እንዳይሰሙ የሚያደርግ ዛር የሰፈረበት ይመስለኛል። ፖለቲከኞቻችን እንተውና የሃይማኖት አባቶች እንኳን ብንመለከት ሱፍ ሲለብሱ ሁሉ ነገራቸው ይቀየራል። በምዕመኑ አንቱታን አትርፈው ይኖሩ የነበሩ ቄስ ፣ ሼክ ወይም የሌላ ሃይማኖት መሪ ሱፍ ሲለብሱ ጨርሰው ግብዝ መሆን ይጀምራሉ። ይህንን አባባል መቶ በመቶ እውነት ነው ባልላችሁም አብዛኛውን ጊዜ ግን ያየሁት እውነት ነው። እናም ይህን ስመለከት ሱፍ ውስጥ የሰፈረው ያለመደማመጥ ዛር ምንድን ነው ብየ እንድጨነቅ ከማድረጉም ባለፈ ለችግሩ መፍትሄ ለማፈላለግም ስለማስብ ብዙ አንቅልፍ መተኛት ካቆምኩ ዘመናት ተቆጥረዋል።

በሰፈራችን ያሉ ሱፍ ለባሾች ለምን መደማመጥ ተሳናቸው ወደሚለው ጥያቄ ማብራሪያ ስመለስ በሰፈራችን ያሉ ሱፍ ለባሾች አብዛኛዎቹ የባህር ዛፍ ፖለቲካ መርህን ስለሚከተሉ ነው። ከእኔ ውጭ ማንንም አላስኖርም የሚል የግብዞች ፖለቲካ !

የእድር መሪዎች የሚመሩት እድር ህልውና በጸና መሰረት ላይ እንዲቀመጥ ከፈለጉ በመጀመሪያ ደረጃ እድሩ ሁነኛ ዓላማ ሊኖረው ይገባል። ዓላማውም በመርህ የተገራ እና በመርህ ሊመራ ግድ ነው። መርህ ደግሞ ዓላማን ለማሳካት መራራም ሊሆን ይችላል። የብዙ እድሮች ተሞክሮ ይሄንን በግልጽ የሚያሳይ ነው። መርህ ደግሞ ለአንድ አድር መሪ «ሀሁ» ነው።

እንደሚታወቀው የእኛ ሰፈር እድር በብዙ ነገሩ ከሰፈራችንም ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ እና ተጽዕኖ ፈጣሪም ነው። በዚህ ሳቢያ የሰፈራችን ሰዎች እንደ እይናቸው ብሌን ቢጠብቁትም የውጭው ዓለም እና የሰፈራችን አንዳንድ እኩይ ተልኮ ይዘው ሚንቀሳቀሱ ሱፍ ለባሾች የእድራችንን ህልውና ሲፈታተኑት እያየን ነው።

በነገራችን ላይ አምባ ገነኖች መርህ አያውቁም። በትቢት ሲወጠሩ ህሊናቸው ግራ እና ቀኙን ፤ ፊት እና የኋላውን ማየት ስለሚያቆም ምድር ላይ ያለ ማንኛውም ሃይል ያለእነርሱ ፈቃድ መኖር እንደማይችል አድርገው ማሰብ ጀምራሉ። በእኔ ልክ የተቀደዱ ለብሶችን ልበስ ! ብለው ማስገደድ ይጀምራሉ። ከዜጎቻቸውም አልፈው የጎረቤት ሀገራትን ሰላም ያውካሉ። ከማወክም አልፈው ወረራ ይፈጽማሉ። ከእነኚህ አይነት ሰዎች መካከለል ናፖሊዮን ቦናፓርት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።

ናፖሊዮን ቦና ፓርት መላ አውሮፓን መግዛት አለብኝ ብሎ ቆርጦ ተነሳ። የሚችለውንም ያህል ወረረ። በዚህ ጊዜ አውሮፓን ናፖሊዮ ቦና ፓርትን ከፈጣሪ በታች ያለ ፈጣሪያቸው እስኪመስላቸው ድረስ አግዝፈው አዩት። ናፖሊዮን ቦናፓርት በበኩሉ ራሱን ከፈጣሪው ጋር አስተካክሎ ተመለከተ። የትኛውም ምድራዊ ሃይል ሊገዳደረኝ አይችልም ሲል ለራሱ ነገረ።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እንደዚህ አይነት መርህ አልባ ግብዝነት ለይስሙላ ፊደል ቆጥረናል የሚሉ ፤ ሳያውቁ ራሳቸውን በአዋቂዎች መርከብ ያሳፈሩ አንዳንድ የእድራችን አስተዳዳሪዎች ፣ ተፎካከሪ ሃይሎች ፣ ማን እንደሚከፍላቸው የማይታወቁ ወግ አሳላጮች እና ጡርምባ ነፊ ሱፍ ለባሾች በከፍተኛ ደረጃ እያስተዋል ነው ። ለዚህም ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በሰፈራችን ሱፍ ለባሾች መካከል መደማመጥ የጠፋው ለመደማመጥ ከመዘጋጀት ይልቅ የባህርዛፍን ፖለቲካ መርህ በማድረጋቸው ነው ያልኩት ።

በድሮ ጊዜ አንዱን ፈላስፋ እንደህ ሲሉ ሰዎች ጠየቁት «ሊያዝኑለት የማያስፈልግ እና የማይገባው ነገር ምንድን ነው?» ፈላስፋውም «የክፉ ሰዎች መሞት!» አለ። በነገራችን ላይ የእድራችን እና የሰፈራችን ሰዎች ሊያዝኑላቸው ከማይችሉት ሰዎች መካከል እድራችን እና ሰፈራችንን በክፍት እያወኩት ያሉትን ሱፍ ለባሾች በሞቱ ጊዜ ስለመሆኑ በአስር ጣቴ እፈርማለሁ ! ብሎ እየተናገረ እያለ ዛሬም አብሿሙ ክንፈ ጉደታ፤ ይልቃል አዲሴ እንዲመልስለት የፈለገው ጥያቄ አዘጋጅቶ ኖሮ ያዘጋጀውን ጥያቄ ለመጠየቅ እጁን በማውጣት ይልቃል አዲሴን በተመስጦ እያደረገው ንግግሩ ላይ አቋረጠው።

የአብሿሙን ክንፈ ጉደታ ጥያቄ እና የይልቃል አዲሴን መልስ በሚቀጥለው ዝግጅታችን ይዘን እንቀርባለን። እስከዚያው አለመደማመጥ ከወለዳቸው የጥፋት ጋሬጣዎች ፈጣሪ ይጠብቀን።

**ሰላም!!!**

# የዘመን ጥበብ

# የለዛ ጥምር ሽልማት

ተገኝ ብሩ




በኪነጥበብ ዕድገት ላቅ ብለው የሄዱ አገራት ለማህበራዊ ለውጥ ትልቅ አስተዋፅኦ የሚያበረክተውን ኪነጥበብ፤ በተለያየ መልኩ ይገለገሉበታል። ማህበረሰባቸውን ለመቅረፅና የተለያዩ በጎ ተፅዕኖዎችን ለመፍጠር እየተጠቀሙበትም ይገኛሉ። አገራቱ ማህበራዊ ፍልስፍናቸውና አገራዊ አስተሳሰብ ከማህበረሰባቸው አልፎ በሌላው ላይ በማንፀባረቅ ብሎም በማስረፅ የሚፈልጉትን ዓላማ ለማሳካትም ችለውበታል። በዚህም አገራዊ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ቀሏቸዋል።

ኪነ ጥበብ የአስተሳሰብ ለውጥ አንዱ መንገድ መሆኑ ቀድሞ ገብቷቸዋልና ለኪነ ጥበብ እድገት አስፈላጊ ነው የሚሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ከዚህ ማሳያዎች መሀከል በዓለምአቀፍ ደረጃ እጅግ የታወቁ ኪነጥበባዊ ሽልማቶችና ማበረታቻዎች መጥቀስ ይቻላል። በእኛም አገር ዘግይቶም ቢሆን ለኪነጥበብ እድገት ትልቅ ሚና ያለው የኪነጥበብ ባለሙያዎችና ስራዎቻቸው መሸለምና ማበረታታት ከተጀመረ ከረምረም ብሏል።

አሁን ላይ በአገራችን በተለያዩ ተቋማት አዘጋጅነት የኪነ ጥበብ ስራዎች ይበረቱ ዘንድ ለኪነጥበብ ባለሙያዎች የሚሰጡ ሽልማቶች ተበራክተዋል። የኪነ ጥበብ ስራዎች እድገት ከፍ ከሚያደርጉት ተግባራት አንዱ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ማበረታታት እና በስራቸው እውቅናና ሽልማት እንዲያገኙ ማድረግ ነው። የኪነጥበብ ባለሙያዎች በስራዎቻቸው እውቅናና የተለያየ ማበረታቻዎችን ማግኘታቸው የሚሰሩት ስራ የተሻለ ለማድረግና በኪነጥበቡ ዘርፍ ጠንክረው በውድድር መንፈስ የተሻሉ ስራዎችን ለመስራት ያስችላቸዋል።

በአገር ደረጃ ለጥበብ ቤተሰቦች ከሚበረከቱ ሽልማቶች ውስጥ ባለፈው ሳምንት ተካሂዶ የነበረው ለዛ ሽልማት አንዱ ነው። የዛሬው የዘመን ጥበብ በዚህ የሙዚቃና የፊልም ስራዎች ተመርጠው የዓመቱ ምርጥ በመሰኘት በተለያየ ዘርፍ የሚሸለሙበት ደማቅ የሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ ያተኩራል።

### የለዛ ሽልማት ከጅማሮ

የኪነጥበብ ባለሙያውን ለማበርታት ብሎም በዘርፉ ያውን ኪናዊ እንቅስቃሴ የተሻለ ደረጃ ላይ ለማድረስ በማሰብ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2003 በአምስት ዘርፎች ሽልማቱን የጀመረው ለዛ አዋርድ በእስከዛሬው ቆይታው ለዘጠኝ ተከታታይ ዓመታት የጥበብ ባለሙያዎችን ሲሸልም ዛሬ ደርሷል። በእርግጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሽልማት ዘርፎቹን እያሰፋና ተሸላሚዎችንም በየመድረኩ እያቀረበ ሲሸልም የቆየው ለዛ ሽልማት ለፊልምና ሙዚቃ ዘርፍ ዕድገት የራሱን አዎንታዊ ሚና ተጫውቷል።

ሽልማት በጀመረበት በ2003 ዓ.ም የዓመቱ ምርጥ ነጠላ ዜማ፣ ምርጥ ተዋናይት፣ የዓመቱ ምርጥ ተዋናይ፣ የዓመቱ ምርጥ ፊልምና የዓመቱ ምርጥ አልበም በሚሉ አምስት ዘርፎች የመጀመሪያው በሸገር ኤፍ.ኤም 102.1 የለዛ ሬዲዮ ፕሮግራም የአድማጮች ምርጫ ሽልማት ሥነሥርዓት በሚል ስያሜ የሀገራችን የኪነጥበብ ሰዎች በተገኙበት በታሪካዊው የብሔራዊ ቴያትር አዳራሽ በደማቁ ተካሂዶ ነበር።

በወቅቱ በአምስት የተለያዩ ዘርፎች ማለትም ዘሪቱ ከበደ "አርቴፊሻያል" በሚለው ነጠላ ሙዚቃዋ፣ ናትናኤል አያሌው (ናቲ ማን) "Man" ብሎ በሰየመው የመጀመሪያ አልበሙ፣ አበበ ባልቻ በሄሮሺማ፣ ራሱ ሄሮሺማ ደግሞ በምርጥ በፊልምነቱ፣ ሰሃር አብዱልከሪም "ያንቺው ሌባ" በተሰኘ ፊልም ላይ ባሳየችው ትወና፣ በየ ውድድር ዘርፎቹ ቀዳሚ አሸናፊዎች ሆነው በለዛ ሽልማት የመጀመሪያዎቹ ተሸላሚዎች ሆነዋል።

በዚህ መልክ በድምቀት የተጀመረው ለዛ ሽልማት ዘንድሮ አምና በኮሮና ምክንያት ባለመካሄዱ የሁለቱን ዓመት ጥምር ሽልማቶች በአንድ ላይ በማድረግ "10ኛውና 11ኛው ለዛ ሽልማት" በሚል ርዕስ ደማቅ የሽልማት መርሀ ግብር በሂልተን ሆቴል ግንቦት 17 ቀን 2014 አድርጓል። በዚህ ዝነኛና ታዋቂ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ባገናኘው መድረክ የሙዚቃና የፊልም ባለሙያዎች በስራዎቻቸው ተመርጠው የላቀ ክብርና ሽልማት ተቀዳጅተዋል።

በሸገር ኤፍ ኤም የለዛ የአድማጮች ምርጫ ሽልማት በሚል መጠሪያ በአምስት ዘርፎች የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን በመሸለም የጀመረው ለዛ ሽልማት ዛሬ ላይ የሽልማት ዘርፉን አሳድጎ፣ የመምረጫ መስፈርቱንም አሻሽሎና አድማጭ ተመልካቹን አሳታፊ ባደረገ መልኩ የ10ኛና የ11ኛ በ12 የተለያዩ ዘርፎች የሽልማት መርሀ ግብሩን ማድረጉም ተገልጿል።

ከውጤት አንፃር ከዚህ በፊት የተሰጡ የሙዚቃና የፊልም ሽልማቶች የላቀ ፋይዳ አስገኝተዋል ለማለትና በትክክል አዎንታዊ ተፅኖአቸውን ለማወቅ ጥናቶችን ማድረግ ቢያስፈልግም፤ ለአርቲስቶች ወይም ለኪነጥበብ ባለሙያዎች የሚሰጡ ሽልማቶች የኪነጥበብ ስራዎቻቸው በተሻለ መልኩ ለተደራሲው ያደርሱ ዘንድ እንደሚረዳቸውና ጥሩ መነሳሳት እንደሚፈጥርላቸው መገመት አይከብድም። የፊልምና የሙዚቃ ባለሙያዎች የሚሰጡት አስተያየትም ለዚሁ ማሳያ ነው።

በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙ የፊልምና የሙዚቃ ባለሙያዎች አስተያየታቸው የሰጡ ሲሆን በየዓመቱ ምርጥ ስራ ለሰሩና በህዝብ ዘንድ የተወደደላቸው እንዲሁም በባለሙያዎች ተመርጠው በዚህ መልክ መበረታታቸው ለኪነጥበቡ እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳለው ገልፀዋል። መሰል ሽልማቶችና ማበረታቻዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል በማለት አስተያየቱን የሰጠው አርቲስት ይገረም ደጀኔ፤ ሽልማቱ አርቲስቶችን ለተሻለ ስራ ያነሳሳል የሚል እምነት እንዳለውም ገልጿል።

በአገራችን በተለያየ ጊዜ የሚዘጋጁ መሰል ሽልማቶች በተለይም በፊልም ስራ ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ ማበርከቱን እንደሚያምን ገልፆ ባለሙያውም በህዝብ ስራው ተወዶለት የክብር ሽልማት ማግኘቱ ለተሻለ ስራ የሚያነሳሳው እንደሆነ ይጠቁማል።

ድምፃዊ ጆኒ ራጋ በበኩሉ የኪነ ጥበብ ሽልማቶች በተለይ ለሙዚቃ መነቃቃት አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዳላቸውና በየጊዜ እየተሰጡ ባሉ ሽልማቶች የሙዚቃ ባለሙያዎቹ ተበራክተው በርካታ ስራዎች ከጥራት ጋር ተመልካች ጋር ማድረስ እዳስቻላቸው አስረድቷል። በለዛ ሽልማት ላይ በርካታ ጊዜ እደታደመ የሚገልፀው ድምፃዊ ጆኒ ባለፉት ሽልማቶች የነበሩ የሽልማት ሂደቶች እና መርሀ ግብሮች በጥሩ መልኩ እንደተመለከተው አስተያየቱን ሰጥቷል።

አርቲስት አለማየሁ ታደሰ በበኩሉ መሰል ሽልማቶች ተጠናክረው መቀጠል እዳለባቸው ገልፆ፤ አርቲስቶች በየዓመቱ በሚሰሩት ስራ መሸለማቸው ብርቱና ጠንካራ እንደሚያደርጋቸው አስረድቷል። በተለይ የሰሩትን ስራ ከአድማጭ ተመልካች ስራህን ወደነዋል ለዚህም መበረታታት ይገባሀል የሚል መልዕክት ማድረሻም እንደሚሆን ገልጿል። ባለሙያውም ሙያዊ አደራውን የሚቀበልበት መድረክ እንደሆነና ህዝቡም በስራህ በርትተህ በዚሁ ቀጥል የሚልበት መድረክ መሆኑን አንስቷል።

### የዚህ ዓመት የለዛ ሽልማት አሸናፊዎች

እጅግ በተዋበ መልኩ በተሰናዳ መድረክ በልዩና ደማቅ በሆነ መልኩ በተካሄደው የሽልማት ሥነ ሥርዓት ላይ በሙዚቃና ፊልም ስራ አንቱ በተሰኙ አርቲስቶች የዓመቱ ምርጥ ተብለው የተመረጡ ባለሙያዎች በክብር ሽልማታቸውን ሰጥተዋል። በዚህ እጅግ የበረታ ፉክክር ተደርጎበታል በተባለው የባለሙያዎችን ስራ መርጦ መሸለም መርሀ ግብር ተሸላሚዎች ወደመድረክ ወጥተው ሽልማታቸውን ተቀብለው፤ ከብርቱ መልዕክታቸው ጋር አጋሮቻቸውን አመስግነውበታል።

በለዛ አዋርድ የዓመቱ ምርጥ ተሰኝተው ለሽልማት የበቁ ስራዎችና ባለሙያዎች የሚከተሉት ነበሩ። በምርጥ ተከታታይ የቴሌቪዥን ፊልም እረኛዬ ድራማ ሲሆን በዚሁ ድራማ የታጨችው ድርብ ወርቅ ሰይፉ በተከታታይ የቴሌቪዥን ፊልም ምርጥ ተዋናይት በመሰኘት ተሸላሚ ሆናለች። ይህ በሶስት እንስት ደራሲያን ተደርሶ በቅድስት ይልማ የተዘጋጀው እረኛዬ የተሰኘው ድራማ ባለፈው ሳምንት በተካሄደው የጉማ ሽልማት ላይ በተለያየ ዘርፍ አሸናፊ ሆኖ መሸለሙ ይታወሳል።

ሌላኛው ብርቱ ፉክክር ተካሂዶበት አሸናፊነቱ የተለየበት በተከታታይ የቴሌቪዥን ፊልም ምርጥ ተዋናይ ዘርፍ የ9ኛው ሺ ሚሊዮን ብርሃኔ ያሸነፈ ሲሆን የዓመቱ ምርጥ ፊልም እንሳሮ በመሆን የለዛ ሽልማት በክብር ተቀዳጅቷል። እንሳሮ የተሰኘው ፊልም በሌሎች የሽልማት መድረኮች እጩ በመሆን ሽልማቶችን የተቀዳጀ ሲሆን ፊልሙ ለእይታ በበቃ በጥቂት ቀናት ውስጥም ተሰርቆ በህገወጥ መንገድ መሰራጨቱ ይታወሳል።

አማኑዔል ሀብታሙ በእንሳሮ ፊልም የዓመቱ ምርጥ የፊልም ተዋናይ በመሆን የተሸለመ ሲሆን ፤ የዓመቱ ምርጥ የፊልም ተዋናይት ዘርፍ መስከረም አበራ በእንሳሮ ፊልም አሸናፊ በመሆን ሽልማት አግኝታለች። ሌላኛው በመድረኩ ላይ ነግሶ የአሸናፊነት ማዕረግ የተቀዳጀው የለዛ ሽልማት የዓመቱ ምርጥ አልበም የዳዊት ፅጌ "የኔ ዜማ" የተሰኘው ዜማ ነው።

የለዛ ሽልማት የዓመቱ ምርጥ ዘፈን መሰሉ ፋንታሁን "ወይ ልማጣ" አሸናፊ ሆና ሽልማቱን ተቀብላለች። የዓመቱ ምርጥ የሙዚቃ ቪዲዮ የጥላሁን ገሰሰ "ቆሜ ልመርቅሽ" የተሰኘው ስራ ተመራጭ ሆኖ ተሸልሟል። የዓመቱ ምርጥ ነጠላ ዜማ በሮፍናን የተዘፈነው (ሶስት) የተሰኘው ዜማ ተሸላሚ ሆኗል። በሌላ ዘርፍ የዓመቱ ምርጥ አዲስ ድምጻዊ ዳዊት ፅጌ በመሆን ሲመረጥ፤ የዚህ ዘርፍ ስያሜም በእውቁ የሙዚቃ ባለሙያው ኤልያስ መልካ ተሰይሟል። የሽልማት ስያሜውም "የኤልያስ መልካ ሽልማት" እንደሚሰኝ ተገልጿል።

በህይወት ዘመን ተሸላሚ በሙዚቃ ኢንዱስትሪው የላቀ አስተዋፅኦ ያበረከተው የሙዚቃ ባለሙያው ሰላም ስዩም በመሆን ተሸላሚ ሆኗል። ሽልማቱም እውቁ ድምፃዊ ማህሙድ አህመድ መድረክ ላይ በመገኘት ለተሸላሚው አበርክቷል። የዓመቱን ምርጥ የተሰኙ የሙዚቃና የፊልም ባለሙያዎችን ያሸለመው ለዛ አዋርድ ከተሸላሚዎች ጋር በተያያዘ የተለያዩ አስተያየቶችን ማስተናገዱም አልቀረም።

### ስለ ሽልማቱ ምን ተባለ?

ባለፈው ዓመት በኮሮና ምክንያት ሳይካሄድ አልፎ ዘንድሮ የሁለቱን ዓመታት ምርጥ የፊልምና ሙዚቃ ስራዎች ብሎ የሸለመው ለዛ ሽልማት በሽልማቱ የተደሰቱትን ያህል ሽልማቱ ከሚገባው አካል ይልቅ የማይገባው ተሰቶበታል የሚል አስተያትም አስተናግዷል። በተለይ የዓመቱ ምርጥ አልበምና የዓመቱ ምርጥ ተዋንያን ዘርፍ የተባሉት በአስተያየት ሰጪዎች የበዛ አስተያየት የተሰጠባቸው ነበሩ።

በእርግጥ መሰል በሆኑ የሽልማት ሂደቶች ውስጥ ከተሸላሚዎች ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ሽልማቶች ተገቢነት ላይ የተቃረኑ አስተያየቶች ከህዝብ መቅረቡ የተለመደ ነው። ለዚህ ዋንኛ ምክንያት ደግሞ ተብሎ በባለሙያዎች በተደጋጋሚ የሚነገረው በሸላሚዎቹ የሚወጡ የመምረጫ መስፈርቶች ብዙውን ጊዜ ለታዳሚው አልያም ለህዝብ ይፋ ባለመደረጉ እንደሆነ ይገለፃል። በመሆኑም በጥበብ ዘርፍ የሚሰጡ ሽልማቶች በሙያተኛውና ህዝብ ዘንድ ብዙ የተጣረሱ አስተያየቶች ሲሰጥባቸው ይታያል።

መሰል አስተያየቶችን ማስቆም ባይቻል እንኳን መቀነስ ያስችል ዘንድ የኪነ ጥበብ ባለሙያው በሰራው ልክ ተሸልሞ በልፋቱና በድካሙ ልክ ማበረታቻ ያገኝ ዘንድ በተለያየ መልኩ መሰል የጥበብ ስራ የሚሰሩ ተቋማት የመምረጫ መስፈርታቸው ለህዝብ ግልፅና የማያሻማ አድርገው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

በእግጥ በእኛ አገር በጀማሪዎቹ የጥበብ ስራ ሸላሚዎች ብቻ ሳይሆን ከኪነጥበብ ዘርፍ ሽልማትና የተለያዩ ማበረታቻዎች ለኪነጥበብ ባለሙያዎቻቸው የሚሰጡ ዓለምአቀፍ ተቋማትም ቢሆን ከተሸላሚው ማንነትና ብቃት ጋር ተያይዞ ከሚነሳባቸው የአመራረጥ ሂደት ጋር በተያያዘ ብዙ ተቃርኖ ይነሳባቸዋል። ነገር ግን ይሄ አልፎ አልፎ የሚገጥም ጉዳይ እንጂ እንደኛው በአሰራር ግልፅነት ምክንያት በየጊዜው ሽልማት ሲካሄድ የሚነሳ አይደለም።

በለዛ የሽልማት መርሀ ግብር ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች መሰል የሽልማት መድረኮች ላይም "በምርጫው ሂደቱ ላይ ሊጠራ ይገባል፤ አመራረጡም ልክ አይደለም።" የሚል አስተያቶች ከተለያዩ አካላት አሉታዊ አስተያየት ይሰጣሉ። ይህንን ለማረምና የአሰራር ግልፅነት ለማስፈን ሸላሚ አካላት ጥረት ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ሸላሚ ተቋማቱ የኪነጥበብ ባለሙያው ለመሸለም እንዲሁም በሙያው ላይ ያሉትን ለማበረታታት በግል እየሰሩት ያለው ጠንካራ ስራ ግን ይበል የሚያሰኝ በመሆኑ ለሽልማቱ አዘጋጆች ከፍ ያለ ምስጋና ሊሰጥም ይገባል።

የኪነ ጥበብ እድገት ማህበረሰባዊ ለውጥን ያፋጥናል። በኪነጥበብ ማስተማር በኪነጥበብ መግራትና ሁለንተናው የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ለማህበረሰባዊ ትስስርና ግንኙነት መጥበቅ ለማህበረሰብ ንቃትና መልከ ብዙ ለውጥ መሰረት የሆነው ጥበብ ዕድገት በቁርጠኝነት መስራት የሚያስልገውም ለዚህ ነው። አበቃን ቸር ይግጠመን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የስራ እድል መስማት ለተሳናቸው ወገኖች

ሰላማዊት ውቤ

የወጣት ሴቶች ማቋቋሚያ ማህበር ከተመሰረተ ሦስት አሥርት ዓመታትን ማስቆጠሩን መሥራቾቹ ይናገራሉ። የተመሰረተበት ዋና ዓላማ ወጣት ሴቶችን የተለያዩ ሙያዎች ባለቤት በማድረግ የየራሳቸውን የገቢ ምንጭ በመፍጠር ኑሯቸውን እንዲደግፉ ማድረግ ነው። አስገድዶ መድፈር በደረሰባቸው ሴት ወጣቶች ላይም ትኩረት አድርጎ በመስራት ላይ ይገኛል።

ይሁንና ማህበሩ ቀስ በቀስ የተመሰረተበትን ዓላማ ሳይለቅ የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ወጣት ሴቶችና ወንዶች በዚሁ ቅኝት መደገፉን ቀጥሎ 30 ዓመታትን አስቆጥሯል። ካለፈው ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለ10 ተከታታይ ቀናት በሚቆየው የቀርከሃ ሥራ ስልጠና 34 መስማት የተሳናቸውን ወጣቶች ካዛንቺስ፣ ባንቢስ የገበያ ማዕከል አካባቢ በሚገኘው የስልጠና ማዕከሉ ውስጥ እያሰለጠነ ይገኛል።

ወጣት እስክንድር መንግስተአብ መስማት ከተሳናቸው ሰልጣኝ ወጣቶች መካከል ሲሆን እሱ በአስተርጓሚው በኩል እንደነገረን ከአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ነው ተመልምሎ የተላከው። ከዚህ ቀደም በምልክት ቋንቋ ስልጠና ወስዶ መስማት የተሳናቸውን፣ ግን ደግሞ በምልክት ቋንቋ የመግባባት ምንም ዓይነት ችሎታ የሌላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች በምልክት ቋንቋ እንዲግባቡ የሚያስችል ስልጠና ሲሰጥ ቆይቷል። ሆኖም ሥራው ኮንትራት በመሆኑ ሲጠናቀቅ ለአንድ ዓመት ያህል ሥራ ፈትቶ ለመቀመጥ ተገዷል።

በዚህ መካከል አሁን እየሰለጠንኩበት ያለው የወጣት ሴቶች ማቋቋሚያ ማህበር ቀድሞ ኮንትራት እሰራበት ለነበረው ተቋም መስማት የተሳናቸው ሥራ አጥ ወጣቶችን መልምላችሁ ስማቸውን ላኩልኝ ሲል እኔን በወረዳ በኩል አቀረበኝ ይላል። ወጣቱ እንደሚለው "ከስምንተኛ እስከ 12ኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ ያላቸው" የሚለውም ከምልመላው መስፈርት አንዱ ነበር።

ወጣቱ ካዛንቺስ በሚገኘው የማሕበሩ ስልጠና ማዕከል መሰልጠን ከጀመረ ሁለተኛ ቀኑን ይዟል። የሚሰለጥነው ደግሞ ከቀርከሃ በሚሰራ የአንፖል ማቀፊያ



ፎቶ ሰላማዊት ውቤ

ወጣት እስክንድር መንግስተአብ



ወጣት ሲዲያ በልሁ

አሰራር ላይ እንደሆነ ነግሮናል። ስልጠናውን እየወሰዱ ያሉት በቡድን በቡድን ሆነው ነው። አንዱ ቡድን ስድስት አንዳንዴም ሰባት አባላት ይኖሩታል፤ እንደ ሁኔታው ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሥራውን ተጋግዘውና ፈጥነው ለመልመድ እያስቻላቸው ይገኛል። በቀጣይ ቀናት የመጽሐፍ መደርደሪያዎችንና ወንበሮችን ጨምሮ ከቀርከሃ በሚሰሩ በተለያዩ ቁሳቁሶች ለመስራት የሚያስችል ስልጠና ይወስዳል። ከስልጠናው በኋላ በቡድን እንደሆኑ በቀርከሃ ሥራ ላይ በተሰማራ ተቋም ተቀጥረው ወይም የራሳቸውን ሥራ በመፍጠር ለመሥራትና ዘላቂ የገቢ ምንጭ ለማግኘት እንዳሰቡ አጫውቶናል።

ሌላዋ የስልጠናው ተሳታፊና መስማት የተሳናት ወጣት ሲዲያ በልሁ ተመልምላ የመጣችው ከነፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ነው። ወጣቷ በ2003 ዓ.ም ከእንጦጦ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በሥዕል ሙያ በዲፕሎማ ተመርቃ ነበር። በሥዕል ሙያዋም በመካኒሳ መስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት በመምህርነት ለአራት ዓመታት አገልግላለች። በርካታ መስማት የተሳናቸውን ወጣቶች በሥዕል ሙያ ማሰልጠን ችላለች። ለጠቅ አድርጋም ቢዲአይኤ የተባለ ድርጅት በመቀጠር እንዲሁ ለአራት ዓመታት ሰርታለች።

ነገር ግን ሥራው ቋሚ ባለመሆኑ ሥራ ፈትታ ከተቀመጠች ዓመታትን አስቆጥራለች። ቋሚ ገቢ የሚያስገኝ የመንግስት ወይም ሌላ ሥራ ለማግኘት ጥረት ብታደርግም አልተሳካላትም። ያለ ሥራ መቀመጡ አሁን በአገራችን ካለው የኑሮ ውድነት፤ በቅርቡ ትዳር መስርታ ከወለደቻቸው ሁለት ልጆች ጋር ተዳምሮ ሲያስቸግራት በቆየችበት ወቅት ይሄ ስልጠና በቴክስት ደረሳት። ሥራው ከሥዕል ጋር ግንኙነት ያለው ቅርፃ ቅርፅ እንደመሆኑ ወደ ማህበሩ መጥታ ተመዘገበችና ስልጠናውን መውሰድ ጀመረች። በአሁኑ ሰዓት ከቀርከሃ ወንበርና ጠረጴዛ፣ የመጽሐፍ መደርደሪያ እንዲሁም የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመሥራት እየሰለጠነች እንደምትገኝ ገልፃልናለች።

«በየቤቱ እኔ ያገኘሁትን ይህን ዕድል ያላገኙ በርካታ መስማት የተሳናቸው ሥራ አጥ ወጣቶች አሉ» የምትለው ሲዲያ ከስልጠናው በኋላ በሙያው ተቀጥራ ወይም የራሷን ሥራ ፈጥራ ዘላቂ የገቢ ምንጭ ከመፍጠር ባሻገር እነዚህን ወጣቶች በቀርከሃ ሥራ ሙያ የማሰልጠን ዕቅድም እንዳላት አውስታለች። ሁሉም ባይሆንም አንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል መስማት የተሳናቸው ሥራ መሥራት አይችሉም በሚል የተሳሳተ ግምት እንዲህ ባለው ስልጠና እንዲሳተፉ አያደርግም። ከግንዛቤ እጥረት ቤተሰቦቻቸውም ከቤት እንዳይወጡ ሁሉ ይከለክሏቸዋል። በመሆኑም ዕድሉን አያገኙም። እነሱን ማሰልጠን ያሰበችውም ለዚህ ነው።

አቶ ታደሰ ተስፋዬ የዛሬ 30 ዓመት የወጣት ሴቶች ማቋቋሚያ ማህበርን ከመሰረቱት አንዱ ናቸው። እኛ ያገኘናቸው መስማት ለተሳናቸው ወጣቶች የቀርከሃ ሙያ ስልጠና ሲሰጡ በመሆኑም የቀርከሃ ሙያ አሰልጣኝ እንደሆኑም ነግረውናል።

እንደ አቶ ታደሰ ለ10 ቀናት በሚቆየው ስልጠና የሚሳተፉት 34 ወጣቶች በሙሉ መስማት የተሳናቸው ናቸው። ቁጥራቸው 34 ያህል ሲሆን ከነዚህ መካከል 16ቱ ሴት መስማት የተሳናቸው ወጣቶች ናቸው። ወጣቶቹ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ ሥራ አጥ ሲሆኑ ከተለያዩ ክፍለ ከተሞች በዚሁ ሥራ አጥነታቸው ተመልምለው በመምጣት ነው ስልጠናው ላይ መሳተፍ የቻሉት። ማህበሩ ስልጠናውን መስማት ለተሳናቸው ወጣቶች ሲሰጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

እየሰለጠኑ የሚገኙት ከቀርከሃ በሚሰሩ የተለያዩ ቁሳቁሶች ሙያ ነው። ለአብነት የቀርከሃ ወንበር፣ የመጽሐፍ መደርደርያ፣ የአንፑል ማቀፊያና ሌሎች ቁሳቁሶች ይጠቀሳሉ። ማህበሩ ስልጠናውን እየሰጠ ያለው መስማት ለተሳናቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥበቃ ከሚያደርገው "ተሀድሶ መስማት የተሳናቸው ማህበር" ጋር በመተባበር እንደሆነም ይናገራሉ።

እንደ አቶ ታደሰ ማብራሪያ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መስማት የተሳናቸው ወጣቶች በተለያየ ምክንያት የሥራ ዕድል ባለማግኘታቸው ዕድሉን እንዲያገኙ ለማድረግ ረጅም ስልጠናዎችን ሊሰጣቸው ዝግጅት እያደረገ ይገኛል። ዋና ዓላማው ወጣቶቹ የነዚህ ሙያዎች ባለቤት ከሆኑ በኋላ የየራሳቸውን የገቢ ምንጭ በመፍጠር ከሥራ አጥነት ተላቅቀውና ራሳቸውን ችለው የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግ ነው። በመሆኑም ተመስርቶ ወደ ሥራ ከገባ ጀምሮ ባለፉት 30 ዓመታት በልብስ ስፌት፣ በቆዳና በተለያዩ ሙያዎች፤ እንዲሁም በስነ-ተዋልዶ 2ሺህ 200 ሴቶችን ማሰልጠንና በሰለጠኑበት ሙያ የየራሳቸውን ሥራ በመፍጠር የገቢ ምንጭ እንዲያገኙ ማድረግ ችሏል። ከነዚህ መካከል 30 ያህሉ አስገድዶ መድፈር የተፈፀመባቸው ናቸው። በተለይ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአገራችን በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ በነበረበት ሰዓት 600 ወጣቶችን በስነ-ተዋልዶ አሰልጥኖና አደራጅቶ በ"ቡና ጠጡ" መርሐ ግብር በሰፊው ወደ ሥራ ያስገባበት ወቅት ነበር።

# ዓለም አቀፍ





## ቱርክ በፊንላንድ እና ስዊድን የኔቶ የአባልነት ጥያቄ ላይ የያዘችውን አቋም እንደማትቀይር አስታወቀች

አዲስ አበባ፣ ቱርክ ለደህንነቷ እና ለኔቶ የወደፊት እጣ ፋንታ ስትል በፊንላንድ እና ስዊድን የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) የአባልነት ጥያቄ ላይ የያዘችውን አቋም እንደማትቀይር አስታወቀች።

የቱርኩ ፕሬዚዳንት ሬሲፕ ታይፕ ኤርዶኻን አገራቱ የኩርድ ሰራተኞች ፓርቲ (ፒ ኬ ኬ) ደጋፊዎች ናቸው በሚል ይወነጅሏቸዋል።

ከዚህ አንጻርም ቱርክ ለራሷ ደህንነት እና ለቃል ኪዳኑ የወደፊት ዕጣ ፋንታ ስትል የአገራቱን አባልነት አትቀበልም ብለዋል።

ቱርክ የኔቶ አባል አገር እንደመሆኗ መጠን በአውሮፓ ህብረት እና በአሜሪካ ጭምር በአሸባሪነት የተፈረጀውን ፒ ኬ ኬን የሚደግፉ አገራትን ከኔቶ አባልነት የመከልከል ሙሉ መብት እንዳላትም አስረድተዋል።

ሽብርተኝነት የሁሉም አባላት ስጋት ስለሆነ አገራቱ ከመቀላቀላቸው በፊት ይህንን እውነታ ሊገነዘቡ ይገባል ማለታቸውን ቲ አር ቲ ዘግቧል።

ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የኔቶ አባል አገራት አስፈላጊ እርምጃዎችን ካልወሰዱ በስተቀር ቱርክ በዚህ ጉዳይ ላይ አቋሟን አትቀይርም ብለዋል ፕሬዚዳንት ኤርዶኻን።

ሁለቱ አገራት ሩሲያ ታጠቃናለች በሚል ስጋት ኔቶን ለመቀላቀል በፈረንጆች ግንቦት 8 ይፋዊ የአባልነት ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፥ የኔቶ አባል አገር የሆነችው ቱርክ ደግሞ አገራቱ አሸባሪ ድርጅቶችን ይደግፋሉ በሚል ጥያቄያቸውን መቃወሟ ይታወሳል።

## አሜሪካ ለዩክሬን በምታደርገው አዲስ የጦር መሣሪያ ድጋፍ ከባድ ሮኬቶችን ልትልክ ነው

አሜሪካ ዩክሬን ራሷን ለመከላከል የሚያስችላትን ዘመናዊ እና ረዥም ርቀት የሚወነጨፉ ሮኬቶችን ልትልክ መሆኑን ፕሬዝደንት ጆ ባይደን አስታወቁ።

ዩክሬን የሩሲያ ኃይሎችን ከርቀት መምታት የሚያስችላት ይህ መሳሪያ እንዲሰጣት ለረጅም ጊዜ ስትጠይቅ ቆይታለች።

የጦር መሣሪያው በሩሲያ ውስጥ ያሉ ነገሮች ኢላማ ሊያደርግ ይችላል በሚል ስጋት አሜሪካ እስካሁን ድረስ የዩክሬንን ጥያቄ አልተቀበለችውም ነበር።

ይሁን እንጂ ረቡዕ ዕለት ፕሬዝደንት ባይደን፣ የጦር መሣሪያው ድጋፍ ኪዬቭ ከሩሲያ ጋር የሚኖራትን የድርድር አቅም ለማጠናከር እና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ግጭቱን ለመፍታት ያስችላል ብለዋል።

"ዩክሬን በጦርነት ቀጠና ውስጥ ወሳኝ ኢላማዎችን ለመምታት የሚያስችላትን ይህንን ዘመናዊ የሆነ ሮኬት እና ተተኳሾች ለመስጠት የወሰነውም በዚህ ምክንያት ነው" ሲሉ ኒው ዮርክ ታይምስ ላይ ጽፈዋል።

አዲሱ የጦር መሣሪያ ድጋፍ መካከል ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችል ረዥም ርቀት መጓዝ የሚችል የሮኬት ሥርዓት እንደሚገኝበት አንድ የዋይት ሃውስ ከፍተኛ ባለሥልጣን የተናገሩ ሲሆን የጦር መሳሪያ ድጋፎች ግን በአሃዝ ምን ያክል እንደሆኑ ግን በቁጥር አልገለጹም።

ይህ የሮኬት ሥርዓት ዩክሬን አሁን ላይ ካላት ከባድ የጦር መሣሪያ በተሻለ በ70 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ኢላማ ላይ ጥቃት መፈፀም ይችላል።

ከዚህ ባሻገር ሩሲያ ካላት ሮኬቶች በተሻለ ኢላማቸውን በትክክል ይመታሉ ተብሎም ይታመናል።

ባለፈው ወር፣ የዩክሬን ጦር አዛዥ ይህን የሮኬት ሥርዓት ማግኘት የሩሲያን የሚሳኤል ጥቃት ለመከላከል ወሳኝ ነው ብለው ነበር።

አሜሪካ ዩክሬን የጦር መሣሪያዎቹን ጦርነቱ በተፋፋመበት እና የዩክሬን ከተሞችን ኢላማ ለማድረግ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ የሩሲያን ከባድ መሣሪያዎች



እና ኃይሎች በሚገኙበት በምስራቃዊ ዶንባስ ክልል ታሰማራለች ብላ ትጠብቃለች።

የዋይት ሃውስ ባለሥልጣናት ሮኬቱን ለዩክሬን ለመስጠት የተስማሙት መሣሪያው በሩሲያ ውስጥ የሚገኙ ኢላማዎችን ለመምታት እንደማይውሉ ከፕሬዝደንት ቮሎዲሚር ዘሌንስኪ ማረጋገጫ በማግኘታቸው ነው።

ባይደን ረቡዕ ዕለት በጻፉት ጽሁፍ "ሩሲያን የሚመታ የሮኬት ሥርዓት ለዩክሬን አንልክም" ብለዋል።

አሁን አሜሪካ ለዩክሬን የምትሰጠው ሮኬቶች ረቡዕ ዕለት በይፋ የተገለጸው 700 ሚሊዮን ዶላር ጥቅል ድጋፍ ዋነኛው ክፍል መሆኑን የዋይት ሃውስ ባለሥልጣናት ተናግረዋል።

ሄሊኮፕተሮች፣ ፀረ ታንክ መሣሪያዎች፣ ስልታዊ የሆኑ ተሽከርካሪዎች እና መለዋወጫዎችም አሜሪካ ጦርነቱ የካቲት ወር ላይ ከጀመረ አንስቶ ለዩክሬን ባደረገችው 11ኛው የጦር ድጋፍ ጥቅል ይካተታሉ ተብሏል።

ረቡዕ ዕለት ባይደን የአሜሪካ ዋና ዓላማ "ዲሞክራሲያዊ፣ ራሷን የቻለች፣ ሉዓላዊ" ዩክሬንን ማየት እንጂ ፕሬዝደንት ፑቲንን ከሥልጣን ማንሳት አሊያም ከሞስኮ ጋር የድንበር ግጭት እንዲፈጠር አይደለም ብለዋል።

ፕሬዝደንቱ "ሩሲያ የሚደረገውን የሰላም ጥረት አልተቀበለችም" ሲሉ የከሰሱ ሲሆን ግጭቱን ለማስቆም ሲባል ዩክሬን የራሷን ግዛት በምላሹ እንድትሰጥ አሜሪካ ጫና እንደማታደርግ ገልጸዋል።

በዩክሬን ጥቅም ላይ እየዋለ ስላለው የኒዩክሌር ጦር መሣሪያ አደጋ አስመልክቶም ፕሬዝደንት ባይደን፤ "ይህ የሩሲያ ፍላጎት መሆኑን የሚያሳዩ እስካሁን ምንም ምልክቶችን አላየንም፤ ነገር ግን ይህንን መጠቀም ተቀባይነት የሌለው እና ከባድ መዘዝ የሚያስከትል" ነው ብለዋል።

የባይደን ጽሁፍ በኒው ዮርክ ታይምስ ላይ ከታተመ በኋላ የሩሲያ የጦር ባለሥልጣናት የአገሪቷ የኒዩክሌር ኃይሎች በሞስኮ አቅራቢያ ኢቫኖቮ ግዛት ልምምድ እያደረጉ መሆኑን ኢንተርፋክስ የዜና ወኪል ዘግቧል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዩክሬን በምስራቃዊቷ ዶንባስ ክልል ጦርነቱ ቀጥሏል።

ማክሰኞ ዕለት የሉሃንስክ ገዥ በክልሉ ከተያዙ ግዛቶች አንዷ የሆነችው ምስራቃዊቷ ከተማ ሴቬሮዶንስክ በአብዛኛው በሞስኮ ቁጥጥር ሥር መዋሏን አስታውቀዋል።

የሩሲያ ኃይሎች በአብዛኛው የሉሃንስክን ግዛት የያዙ ሲሆን ጎረቤቷን ዶኔስክ ለመያዝ ትኩረት እያደረጉ መሆናቸውም ተነግሯል።

**ምንጭ ቢቢሲ**

# ስፖርት



# ሉሲዎቹ በሴካፋ የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ዛሬ ያደርጋሉ

**ብርሃን ፈይሳ**




በሴካፋ የሴቶች ዋንጫ ኢትዮጵያን እየወከለ የሚገኘው የብሄራዊ ቡድን አባላት፤

የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ሀገራት የሴቶች እግር ኳስ ውድድር (ሴካፋ) ትናንት በአዘጋጇ ዩጋንዳ እና ሩዋንዳ ጨዋታ ተጀምሯል። ስምንት ሀገራት በሁለት ምድብ ተደልድለው ለአሸናፊነት በሚፋለሙበት በዚህ ውድድር ዛሬ ሁለት ጨዋታዎች ይደረጋሉ። በዛሬው የጨዋታ መርሃ ግብር መሰረትም በምድብ ሁለት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን (ሉሲዎቹ) ከዛንዚባር አቻቸው ጋር ሲገናኙ፤ በሌላኛው ጨዋታ ደግሞ ታንዛኒያ ከደቡብ ሱዳን ጋር ይጫወታሉ።

12 አባል ሀገራት ያሉት የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ እግር ኳስ ማህበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት የሚካሄደው ይህ ውድድር በአህጉሪቱ ረጅም ዓመታትን በማስቆጠር ቀዳሚው ነው። ውድድሩ በሁለቱም ጾታ በተለያየ የዕድሜ ገደብ የሚካሄድ ሲሆን፤ የሴቶቹ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ እአአ 1986 በዛንዚባር አዘጋጅነት ነበር የተካሄደው። ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ተቋርጦ በመቆየት እአአ በ2016 በድጋሚ ተጀምሯል። በ2018 እና 19 በተከታታይ ከተካሄደ በኋላም ለ2021 ጅቡቲ እንድታስተናግድ ቢደረግም በድጋሚ ሊሰረዝ ችሏል። በመሆኑም ለአምስተኛ ጊዜ የሚደረገውን የሴካፋ ሴቶች ዋንጫ ኡጋንዳ ለሁለተኛ ጊዜ የማሰናዳት ዕድሉን አግኝታለች። ትናንት በተጀመረው በዚህ ውድድር ላይም በመጀመሪያው ምድብ አዘጋጇ ኡጋንዳ ከሩዋንዳ ጋር ስትጫወት፤ የብሩንዲ እና ጅቡቲ ብሄራዊ ቡድኖችም ተገናኝተዋል።

ዛሬ ሁለተኛ ቀኑን በያዘው በዚህ ውድድርም በምድብ ሁለት ኢትዮጵያ ከዛንዚባር፤ ታንዛኒያ ደግሞ ከደቡብ ሱዳን ይጫወታሉ። በአሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል እየተመራ ያለው የኢትዮጵያ ሴቶች ብሄራዊ ቡድን (ሉሲዎቹ) ከትናንት በስቲያ ወደ ውድድሩ ስፍራ ማቅናታቸው የሚታወቅ ነው። የሴካፋ ከ20 ዓመት በታች ሴቶች አሸናፊና ለዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ብሄራዊ ቡድን እስከመጨረሻው ዙር በማድረስ ተስፋ ያሳየው ወጣቱ አሰልጣኝ ቡድኑ በውድድሩ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ መዘጋጀቱን አረጋግጧል። አስቀድሞ ሲመራው የቆየው የታዳጊዎች ቡድን ውድድሩን በዩጋንዳ ማድረጉን ተከትሎ ስለሜዳው፣ አየሩ እንዲሁም ስለቡድኖቹ አስቀድሞ መረጃው ያለው መሆኑ ለዚህ ውድድር እገዛ የሚያደርግለት መሆኑንም አስገንዝቧል።

አሰልጣኙ ከጉዞው አስቀድሞ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይም በወጣት ተጫዋቾች የተዋቀረ ቡድን ይዞ በውድድሩ ላይ እንደሚካፈልም ጠቁሞ ነበር። ቡድኑን የመምራት ኃላፊነት ከፌዴሬሽኑ መረከቡን ተከትሎ በሊጉ ላይ ጥሩ እንቅስቃሴ ካላቸው ጥቂት ተጫዋቾች እንዲሁም ከ20 ዓመት በታች ብሄራዊ ቡድን በርካታ ተጫዋቾችን (13 ተጫዋቾችን) በማሰባጠር ቡድኑን መስርቷል። ይህንንም ያደረገበት ምክንያት በወጣቶች የተገነባና ለረጅም ጊዜ ግልጋሎት የሚሰጡ ተጫዋቾች ያሉት ብሄራዊ ቡድን እንዲኖር እንዲሁም ውድድሩ ለወጣት ተጫዋቾች ጥሩ ማሳያ ስለሆነ ቅድሚያ ለመስጠት መሆኑንም ገልጿል። አብዛኛዎቹ ተጫዋቾች በውድድር ላይ የቆዩ በመሆኑ ከግንቦት 10/2014 ዓ.ም ጀምሮ ተጫዋቾቹ ተሰባስበው በቀን አንዴ ልምምድ በመስራት ቡድኑን በማዋሃድ ላይ ትኩረት ሲያደርጉ ቆይቷል። ከ23ቱ ተጫዋቾችም ጉዳት ያስተናገዱት ሁለት ተጫዋቾች ማገገማቸውንና የተቀሩትም በመልካም ጤንነት ላይ የሚገኙም ናቸው።

34 ልኡካንን ያቀፈው ቡድኑ ሁለት ሰዓት በሚጠጋ በረራ ኡጋንዳ የደረሰ ሲሆን፤ ትናንት ረፋድ ላይ በጂንጃ ትምህርት ቤት ሜዳ የመጀመሪያ ልምምዱን ሰርቷል። ሉሲዎቹን የሚገጥመው የዛንዚባር ብሄራዊ ቡድን(የዛንዚባር ንግስቶች) የመጀመሪያውን ዋንጫ በሀገሩ ማስቀረት የቻለ ነው። በአንጻሩ በቀጣዮቹ ውድድሮች በከፍተኛ ልዩነት በመሸነፉ ከውድድር ውጪ በመሆን የዋንጫ ጉዞውን ለማሳካት አልቻለም።

ሉሲዎቹ እአአ በ2016 እና 2018 የሴካፋ ተሳትፏቸው ሶስተኛ ሆነው ያጠናቀቁበት ውጤት ትልቁ ሆኖ ተመዝግቦላቸዋል። ሁለተኛውን ጨዋታ ግንቦት 27/2014ዓም ከታንዛኒያ ጋር የሚያደርጉ ሲሆን፤ ግንቦት 29/2014ዓም ደግሞ ከደቡብ ሱዳን ጋር የምድቡን የመጨረሻ ጨዋታ ያከናውናሉ። የግማሽ እና የፍጻሜ ጨዋታዎቹም ሰኔ 02 እና 04/2014ዓም የሚደረግ መሆኑንም የተያዘው መርሃ ግብር ያመላክታል።


## የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት፡ Aktiebolaget SKF አድራሻ: 415 50 Gothenburg, Sweden
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/ 3257
3. የጥበቃ ጊዜው፡ 23/05/2021 እስከ 22/05/2028
4. የንግድምልክት፡ SKF

5.ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 13/12/2007 Vol.LXXIV No.343 እና በኢትዮጵያ ሄራልድ በቀን 14/8/2015 Vol.LXXI No.290 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው፡፡
6.ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛዉም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሮአዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL. LXXXI NO. 265 - 25 /9/2014 (2/6/2022)

## የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም- ሴሉላሪቲ ኢንክ (Celularity, Inc,) አድራሻ፡ (170 Park Avenue, Florham Park, New Jersey 07932 United States.)የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/5887/15
3. የጥበቃ ጊዜው፡ ከ 23/02/2022 እስከ 23/02/2029
4. የንግድ ምልክት፡ BIOVANCE
5. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 10/04/2008 ዓ.ም በ Vol LXXV No. 100 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው ፡፡
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL. LXXXI NO. 265 - 25 /9/2014 (2/6/2022)

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| 1. ስም:- ቼሚኖቫ ኤ/ኤስ (Cheminova A/S) አድራሻ: Thyborønvej 78, 7673 Harboøre, Ronland, Denmark | |
| 2. ማመልከቻ ገቢ የሆነበት ቀን | 19/04/2022 |
| 3. የማመልከቻ ቁጥር | FTM/13342/22 |
| 4. የንግድ ምልክቱ መግለጫ | የቃል |
| 5. የንግድ ምልክቱ | DANADIM |
| አለም አቀፍ ምድብ | 05 |
| ማመልከቻው የሚሸፍናቸዉ ምርቶች:- ምድብ 05:- ኢንሴክቲሳይዶችን ማምረት ነው፡፡ | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰውን የንግድ ምልክት በምዝገባ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን ካልቀረበ በስተቀር ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናሳውቃለን።

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL. LXXXI NO. 265 - 25 /9/2014 (2/6/2022)

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| ስም:- ኤፍ ኤም ሲ አግሪካልቸራል ሶሉሽንስ ኤ/ሲ (FMC Agricultural Solutions A/S) አድራሻ:- Thyborønvej 78, 7673 Harboøre, Ronland, Denmark | |
| 1. ማመልከቻ ገቢ የሆነበት ቀን | 03/05/2022 |
| 2. የማመልከቻ ቁጥር | FTM/13395/22 |
| 3. የንግድ ምልክቱ መግለጫ | የቃል |
| 4. የንግድ ምልክቱ | FYFANON |
| 5. አለም አቀፍ ምድብ | 05 |
| ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች: ምድብ 05:-- ኢንሴክቲሳይዶችን ማምረት ነው፡፡ | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰውን የንግድ ምልክት በምዝገባ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ በስተቀር ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOL. LXXXI NO. 265 - 25 /9/2014 (2/6/2022)

# አማራ ክልል

ንብረትነቱ የጌታቸው መሀመድና አህመድ አደም የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ኮድ 52045 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በ4/9/14 በተፃፈ አመልክተዋል። ሰሌዳውን ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአብክመ ትራንስፖርት ሉጅስቲክ ባለሥልጣን**
**የደቡብ ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት**

# ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረት ስም አቶ አማረ ጥላሁን አለሙ የሰሌዳ ቁጥር 3-49200 ኦሮ የተሽከርካሪው የኋላ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብሎ በቀን 16/09/2014 ዓ.ም. አመልክቷል። በመሆኑም ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲቀርብ ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን።

**የገላን ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ባለሥልጣን**

የባለንብረቱ ስም አቶ ደበበ ጌቱ የሰሌዳ ቁጥር 2 ኦሮ 87837 የሊብሬ ቁጥር 0226639 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ወድቆ ጠፋብኝ ብለው በ 11/09/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የመኪናው ሰሌዳ ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ምትክ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የምስራቅ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

# አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም የኢትዮ/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የሰሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-11823 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JTFAG426X0-005662 ሞዴል TOYOTA RZN. 147L-TRMDS የሞተር ቁጥር 1RZ-3345229 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ17/9/2014 አመልክተዋል ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም የማነ ግርማይ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A19044 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር AHTFR29G707043501 ሞዴል KUN25L-PRMDHV የሞተር ቁጥር 2KDA64927 የሊብሬ ቁጥር 358817 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 16/9/2014 አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

ባለንብረት ስም ደረጀ ጌታሁን ይልማ ሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A53634 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JTDKK183500108872 ሞዴል SCP10-AHMGKW የሞተር ቁጥር 1SZ-0256091 የሊብሬ ቁጥር 371246 ላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 17/9/2014 አመልክተዋል። ሰሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**